ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ዓርብ

81ኛ ዓመት ቁጥር 203 መጋቢት 23 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




## «ፖለቲካዊ መፍትሔ የሚሹ ችግሮችን ለመፍታት አገራዊ ምክክሩ እንደ አንድ መሠረታዊ እርምጃ ተደርጎ ሊወሰድ ይገባል»

**ኮሚሽነር ዶክተር ዳንኤል በቀለ**
**የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ኮሚሽነር**

ሞገስ ጸጋዬ

አዲስ አበባ:- ፖለቲካዊ መፍትሔ የሚሹ ችግሮችን ለመፍታት አገራዊ ምክክሩ እንደ አንድ ትልቅ መሠረታዊ እርምጃ ተደርጎ ሊወሰድ ይገባል ሲሉ የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን (ኢሰመኮ) ኮሚሽነር ዶክተር ዳንኤል በቀለ አስታወቁ፡፡

የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን (ኢሰመኮ) ኮሚሽነር ዶክተር ዳንኤል በቀለ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በአገራዊ ምክክሩ አማካኝነት ፖለቲካዊ መፍትሔ የሚሹ ችግሮችን ለመፍታት እንደ አንድ ትልቅ መሠረታዊ እርምጃ ተደርጎ ሊወሰድ ይገባል። አገራዊ ምክክሩ ችግሮች ለመቅረፍ ተስፋ አለው ሲሉ አስረድተዋል፡፡

በኢትዮጵያ ውስብስብ የሆነ የፖለቲካና የሰብዓዊ መብት ቀውስ አለ ያሉት ኮሚሽነሩ፤ ችግሩ የፖለቲካ ቀውስና የሰብዓዊ መብት ጥሰት ብቻ ሳይሆን የጤና፣ የኢኮኖሚ፣ የትምህርትና መሰል ችግር መሆኑን ገልጸዋል። የተጀመረው የአገራዊ ምክክር መድረክ ካሉብን ችግሮች

«ፖለቲካዊ መፍትሔ .. ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች በመግለጫው:-

## - ድርቁን አሳሀ እንዲያነሳ በአገር ሰላም እንዲሰፍን መጸለይ ያስፈልጋል
## - የተፈናቀሉትን መደገፍ፣ የከፋቸውንና ያዘኑትን ማጽናናት ይገባል
## - ረመዳንን ለማክበር የሚመጡ እንግዶችን ለመቀበል ዝግጅት መደረጉን አስታውቀዋል

ዘላለም ግዛው

አዲስ አበባ:- 1443ኛው የረመዷን ጾም ወቅት፤ በሰላም፣ በመተሳሰብና በመከባበር ማሳለፍ ይገባል ሲሉ የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ተቀዳሚ ሙፍቲ ሐጂ ኡመር ኢድሪስ ገለጹ። ረመዳንን ለማክበር የሚመጡትን እንግዶች ለመቀበል ዝግጅት እየተደረገ እንደሚገኝም ተጠቁሟል።

ጨረቃ እንደታየ ነገ ቅዳሜ ወይንም ከነገ ወዲያ እሁድ የሚገባውን 1443ኛውን የረመዷን ጾምን አስመልክቶ ትናንት መግለጫ የሰጡት ተቀዳሚ ሙፍቲ ሃጂ ኡመር ኢድሪስ፤ ለሕዝበ ሙስሊሙ የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡

ረመዷን የምህረት፣ የመከበሪያና የማክበሪያ ወር ነው፡፡ ጾሙን ያለጭቅጭቅ፣ ያለጥላቻ ማሳለፍ ይገባልም ብለዋል፡፡ ፈጣሪ እንድንጣላ፣ እንድንቃረን አይፈልግም፤ ጭቅጭቅን በማስወገድ፣ በሰላም፣ በስግደት ረመዷንን እንድትጨርሱ አደራ ለማለት እወዳለሁ ሲሉም መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡

እንደርሳቸው ማብራሪያ፤ ያለፉት ሁለት ዓመታት በበሽታ፣ በጭንቀት አልፈዋል፣ በቀጠለው ጦርነት አንዱ ሌላውን በማፈናቀል ከርመናል፡፡ በወሎ፣ በአፋር፣ በወለጋ ያሉ ወንድሞቻችን እህቶቻችን፣ የሃይማኖት አባቶች በስደት ላይ ይገኛሉ፣ ሃይማኖታዊ ትምህርትም

የኢትዮጵያ .. ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ: ገበቦ ገብሬ









## በአፋር ክልል በአብኣላ በኩል እርዳታ ወደ ትግራይ ክልል መጓጓዝ ጀመረ

ገጽ 4



ፎቶ:በሏይ አሰፋችው

## «ምክክሩ በመቃብራችን ላይ ይባሉ የነበሩ አጀንዳዎች ለውይይት የሚቀርቡበት በመሆኑ ከምንም በላይ አስፈላጊ ነው»

-አቶ የሽዋስ አሰፋ
የኢዜማሊቀመንበር

ገጽ 4









አቶ ዮሐንስ ንጋቱ

## ማኅበሩ የዓለም አቀፍ አካውንታንቶች ፌዴሬሽን አባል ለመሆን እየሠራ ነው

**ውብሸት ሰንደቁ**

<u>አዲስ አበባ፡-</u> የኢትዮጵያ ሒሳብ አዋቂዎችና ኦዲተሮች ማኅበር የዓለም አቀፍ አካውንታንቶች ፌዴሬሽን አባል ለመሆን እየሠራ መሆኑን የድርጅቱ ፕሬዚዳንት አቶ ዮሐንስ ንጋቱ ገለፁ፡፡

በትላንትናው ዕለት የኢትዮጵያ ሒሳብ አዋቂዎችና ኦዲተሮች ማኅበር ዓመታዊ ስብሰባና የማኅበሩ 50ኛ ዓመት የምሥረታ በዓል በተካሄደበት ወቅት አቶ ዮሐንስ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት ዓለም አቀፍና አገር አቀፍ ሁኔታዎች አስገዳጅ እየሆኑ በመምጣታቸው ማኅበሩ የዓለም አቀፍ አካውንታንቶች ፌዴሬሽን አባል ለመሆን የተለያዩ ሥራዎችን እያከናወነ ነው፡፡

ማኅበሩን የዓለም አቀፍ አካውንታንት ፌዴሬሽን አባል ለማድረግ ለአባልነት የሚያስፈልጉ መሥፈርቶችን እየተሟሉ እንደሆነና በሚቀጥለው አንድ ዓመት ውስጥ ቀሪ ሥራዎችን ተጠናቀው የዓለም አቀፍ አካውንታንቶች ፌዴሬሽን አባል ለመሆን ዕቅድ ይዘው እየተንቀሳቀሱ እንደሆነም ገልጸዋል፡፡

የኢትዮጵያ ሒሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ ባወጣው መመሪያ መሠረት ከዚህ በኋላ መሠል ማኅበራት በኢትዮጵያ ውስጥ መንቀሳቀስ የሚችሉት የዓለም አቀፉ አካውንታንቶች ፌዴሬሽን አባል የሆኑና አባል ለመሆን ሂደቶችን የጀመሩ ብቻ እንዲሆኑ ተወስኗል፡፡

ስለዚህም በማኅበርነት መቀጠል የምንችለው የዚህ ዓለም አቀፍ ድርጅት አባል መሆን ስንችል ብቻ በመሆኑ ሰፋፊ ሥራዎችን እየሠራን ነው ሲሉ አብራርተውልናል፡፡

የዓለም አቀፍ ድርጅቱ አባል መሆን ያለውን ጠቀሜታ አስመልክቶም የኢትዮጵያ ሒሳብ አዋቂዎችና ኦዲተሮች ማኅበር አባላት በየትኛውም አገር ሄደው እንዲሠሩ የሚያስችልና እና ራሳቸውን እንዲለውጡ የሚረዳ ነው ብለዋል፡፡

በሙያው ውስጥ የሚተገበሩ ዓለም አቀፍ ደረጃዎችን በአገር ውስጥ አሠራር ተግባራዊ ለማድረግም አጋዥ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

በአገሪቱ በሒሳብ አያያዝ ላይ ያለው የኅብረተሰቡ እና የድርጅቶች ግንዛቤ እምብዛም እንደሆነ የገለጹት የማኅበሩ ፕሬዚዳንት በማኅበረሰቡ ዘንድ ሙያው ሒሳብ መመዝገብ ብቻ ተደርጎ እንደሚቆጠርና በድርጅቶችም ዘንድ ሰፋ ያለ ግንዛቤ እንደማይታይ አብራርተዋል፡፡

ድርጅቶችም ሒሳብ በባለሙያ የሚያሠሩት በመንግሥት አስገዳጅ ሁኔታዎች ሲጣሉባቸው መሆኑን በማሳያነት አንስተዋል፡፡

ሒሳብ አያያዝ ከሒሳብ መያዝም በላይ ስላለው ጠቀሜታ ማሳወቅ እንደሚጠበቅና ይህም የማኅበራቸው አንዱ ኃላፊነት እንደሆነ ገልፀው የሒሳብ ሪፖርቶች ገቢና ወጪን ከማሳወቅ በተጨማሪ ኢንቨስተሮች አዋጭ ኢንቨስትመንት ላይ መሆናቸውን ለመመዘን፤ የአንድን ድርጅት ሕልውና ተገማች ለማድረግ፤ ከተቋቋሙ ድርጅቶች እና ኢንቨስትመንቶች ላይ ድርሻ ለመሸጥ እንዲሁም ለውሳኔ ሰጪ አካላት ጠቃሚ እንደሆነ አብራርተዋል፡፡

የኢትዮጵያ ሒሳብ አዋቂዎችና ኦዲተሮች ማህበር 1 ሺህ 400 አባላት እንዳሉት እና 50ኛ ዓመቱን አስመልክቶ የሚካሄዱ የፓናል ውይይቶች፣ ሩጫዎች፣ ስፖርታዊ ውድድሮች እና ባህላዊ ጨዋታዎች እስከ ሰኔ 30 ቀን 2014 ዓ.ም ድረስ የሚቀጥሉ መሆኑን ከማኅበሩ ያገኘነው መረጃ ያመለክታል።

## "እህል ጫኝ መኪናዎቻችን ያለ አግባብ ታስረውብናል"

**- ባለንብረቶች**

## ‹‹መኪናዎችን ያሰርነው በወቅቱ መረጃ ማቅረብ ባለመቻላቸው ነው"

**- አዲስ ከተማ ክፍለከተማ**

**ዳግማዊት ግርማ**



<u>አዲስ አበባ፡-</u> እህል ጫኝ መኪናዎቻችን ያለ አግባብ ታስረውብናል ሲሉ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ልዩ ስሙ እህል በረንዳ በሚባለው አካባቢ ተሰማርተው የሚገኙ ባለመኪናዎች ገለጹ፡፡ ክፍለከተማው በበኩሉ መኪናዎችን ያሰርነው በወቅቱ መረጃ ማቅረብ ባለመቻላቸው ነው ያለ ሲሆን፤ ሕጋዊ መኪኖችን እያጣራ እንደሚለቅም ገልጿል፡፡

እህል ከክፍለ ሀገር ወደ አዲስ አበባ በመኪና አምጥተው የሚያከፋፍሉ ነጋዴዎች እህል ጫኝ መኪናዎቻቸው ያለ አግባብ እንደታሰሩባቸው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ቅሬታቸውን አቅርበዋል፡፡

እህል የጫነ መኪና ታስሮበት መንቀሳቀስ እየቻለ እንዳልሆነ የገለጸው አቶ ሞገስ ታምራት ፤ የአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ መኪናዎቻቸውን ያለ አግባብ ሰብስቦ በማሰሩ ምክንያት የመኪና ባለንብረቶች ለአላስፈላጊ እንግልት ተዳርገዋል ብሏል፡፡

የመኪናዎቹን ሕጋዊነት ለማረጋገጥ ማስረጃ ይዘው መቅረባቸውን የጠቆመው አቶ ሞገስ፤ የነሱም መኪና ሕጋዊ ደረሰኝና ንግድ ፍቃድ ያለው ቢሆንም እንደታሰረባቸው ተናግሯል፡፡

አቶ ሞገስ ለቅሬታቸው ምላሽ የሚሰጥ አካል ማግኘት እንዳልቻሉና እህል ጫኝ መኪኖቹን በሚመለከት የጠፋው ጥፋት ምን እንደሆነ የሚያሳውቅ ኃላፊነት የሚሰማው አካል ማግኘት እንዳልቻሉም ተናግረዋል፡፡

ሕጋዊ ያልሆኑ ሰዎችን ማጣራት መልካም መሆኑን የጠቆሙት አቶ ሞገስ ሕጋዊ አካልነት ኖሮት ንግድ ፍቃድ ያለውን ግብር የሚከፍልን ሰው መኪና አስሮ እንዳይንቀሳቀስ ማድረግ አግባብነት የሌለውና ያለውን የኑሮ ውድነት የሚያባብስ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ቅሬታቸውን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ካቀረቡት ውስጥ አንዱ የሆኑት አቶ ወንድወሰን አያሌው በበኩላቸው የክፍለሀገር ነጋዴዎች እየላኩላቸው እህሎችን እንደሚሸጡ ገልጸው መኪናዎቹ በመታሰራቸው ምክንያት የሥራ እንቅስቃሴያቸው መስተጓጎሉን ተናግረዋል፡፡ ‹‹አጣርተን እንለቃችኋለን›› የሚል ምላሽ ቢሰጣቸውም መፍትሔ እንዳላገኙ ገልፀዋል፡፡

ኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ለቅሬታው ምላሽ እንዲሰጡት ጥያቄ ያቀረበላቸው የአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የንግድ ክትትልና ቁጥጥር ባለሞያ የሆኑት አቶ ዋሲሁን አዱኛ በበኩላቸው እንደገለፁት እህል ጫኝ መኪናዎቹ መጀመሪያውኑ የቆሙት ከእህል በረንዳው ቅጥር ውጭ ሲሆን፤ ስፍራውም መቆም የተከለከሉበትና ሕገወጥ ስፍራ ነው፡፡

የመኪናዎቹ መያዝ ያለውን የዋጋ ንረት አያባብሰውም ወይ ሲል የኢትዮጵያ ፕሬስ ላቀረበላቸው ጥያቄ ምላሽ የሰጡት አቶ ዋሲሁን የእህል ጫኞቹ መኪናዎች መያዝ በምንም መልኩ ንረቱን እንደማያባብስና ይልቁንም ሕጋዊ ሳይሆኑ ሥራውን አየር ባየር የሚሠሩ ሕገወጦችን አደብ የሚያስገዛ እርምጃ መሆኑንም ተናግረዋል፡፡

## የሃይማኖት መገናኛ ብዙኃን በጎ ዕሴቶችን በማጠናከር ለአገር አንድነት የበኩላቸውን ሚና እንዲወጡ ጥሪ ቀረበ

- ባለስልጣኑ ለሃይማኖት መገናኛ ብዙኃን ከመጋቢት 23 ጀምሮ ፈቃድ መስጠት ሊጀምር ነው

**ሞገስ ተስፋ**

<u>አዲስ አበባ፡-</u> የሃይማኖት መገናኛ ብዙኃን ለሕዝብ መፈቃቀር፣ አብሮነት፣ መረዳዳት፣ ሰላም የመሳሰሉትን በጎ ሃይማኖታዊ ዕሴቶችን በማጠናከር ለአገር አንድነት የበኩላቸውን ሚና እንዲወጡ የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ባለስልጣን አሳሰበ፡፡ ባለስልጣኑ ለሃይማኖት ብሮድካስት መገናኛ ብዙኃን ከመጋቢት 23 ጀምሮ ፈቃድ መስጠት ሊጀምር መሆኑን አስታውቋል፡፡



የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ባለስልጣን የሃይማኖት ብሮድካስት ረቂቅ መመሪያን አስመልክቶ በተዘጋጀው የባለድርሻ አካላት የውይይት መድረክ ላይ የባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር አቶ መሐመድ ኢድሪስ እንደገለጹት፤ የሃይማኖት መገናኛ ብዙኃን ለሕብረተሰቡ በተለይም ለሃይማኖቱ ተከታዮቻቸው ተደራሽ በመሆን ሃይማኖታዊ አስተምሯቸውን በተገቢው ሁኔታ እንዲያደርሱ የሚያስችል ነው፡፡

እንደ ዋና ዳሬክተሩ ገለጻ፤ በኅብረተሰቡ ዘንድ የሃይማኖት መርሐ ግብር በቴሌቪዥን ለመከታተል ከነበረው ፍላጎት ጋር በተያያዘ አገራዊ ለውጡን ተከትሎ የሃይማኖት ብሮድካስተሮች በሕግ ዕውቅና እንዲያገኙ፤ የመገናኛ ብዙኃን ፖሊሲውም ሆነ የአዋጅ ማሻሻያ በመደረጉ ባለስልጣኑ ፈቃድ አውጥተው እንዲንቀሳቀሱ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፡፡

ቀደም ባለው የመገናኛ ብዙኃን መመሪያ የሃይማኖት መገናኛ ብዙኃን ብሮድካስት እንዳያቋቁሙ፣ ሕጋዊ እውቅና እና ፈቃድ እንዳያገኙ ተከልክለው መቆየታቸውን ያስታወሱት ዋና ዳይሬክተሩ፣ በተሻሻለው የመገናኛ ብዙኃን አዋጅ የሃይማኖት ብሮድካስት በመገናኛ ብዙኃን አዋጅ 1238/2013 በተደነገገው መሠረት ባለስልጣኑ ከመጋቢት 23 ጀምሮ ለነባርም ሆነ ለአዳዲስ የሃይማኖት ቴሌቪዥን ፈቃድ አመልካቾች ፈቃድ መስጠት ይጀመራል ብለዋል።

በተደረገው ጥናት መሠረት በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ከ50 በላይ የሃይማኖት ቴሌቪዥን ጣቢያዎች በስርጭት ላይ እንደሚገኙ የገለጹት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ጣቢያዎቹ ሃይማኖታዊ መልዕክቶችን በማስተላለፍ ለተከታዮቻቸው አማራጭ የመገናኛ ዘዴ በመሆን እያገለገሉ እንደሚገኙ ዋና ዳይሬክተሩ ተናግረዋል፡፡

በአንጻሩ ጥቂት የሚባሉ በኃላፊነት ስሜት እና በጥንቃቄ የማይንቀሳቀሱ የሃይማኖት ሚዲያዎች በመኖራቸው በሚያሰራጯቸው መረጃዎች ከኅብረተሰቡ የሚደርሱ ከሕግ፣ ከሞራል፣ ከጤና ጋር የሚቃረኑ ንግግሮችን የማሰራጨት እና ሌሎች ሃይማኖቶችን የመንቀፍ ቅሬታዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመሆኑ ከዚህ ድርጊታቸው ሊታቀቡ እንደሚገባ አሳስበዋል፡፡

የሃይማኖት መገናኛ ብዙኃን ለአገር አንድነት፣ ለሕዝብ መፈቃቀር ፣ አብሮነት፣ መረዳዳት፣ ሰላም እና መሰል በጎ ሃይማኖታዊ ዕሴቶችን በማጠናከር የበኩላቸውን ሚና አጠናክረው እንዲቀጥሉ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

የመገናኛ ብዙኃን ባለስልጣን ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ግዛው ተስፋዬ በበኩላቸው፣ የሃይማኖት ብሮድካስት ረቂቅ ሕግ ማዘጋጀት ያስፈለገው አዋጁን ተግባራዊ ለማድረግ ነው፡፡ ለዚህም የፈቃድ አሰጣጥ ሥርዓቱን ግልጽና ፍትሐዊ ለማድረግ ሲባል ረቂቅ መመሪያው እንደተዘጋጀ ገልጸዋል፡፡

የሃይማኖት ብሮድካስተሮች ፍቃድ የሚሰጣቸው የሃይማኖት ተቋም ሆነው የሃይማኖት ብሮድካስት ሚዲያ ለማቋቋም ፈቃድ ሲጠይቁና በሚመለከተው የሃይማኖት ተቋም ፈቃድ ሲያገኙ ነው፡፡

የመገናኛ ብዙኃን አዋጅ አንቀጽ 70 ላይ እንደተደነገገው የብሮድካስት ሚዲያዎችን መብትና ግዴታ ያስቀመጠና የሃይማኖት ብሮድካስተሮች ማሟላት ያለባቸውን መብትና ግዴታ በዝርዝር ያስቀመጠ መሆኑን አቶ ግዛው ገልጸዋል። ፈቃድ ከተሰጣቸው በኋላም ባለስልጣኑ አስፈላጊውን ድጋፍና ቁጥጥር ያደርጋል፡፡ መመሪያው ተገቢ ስለመሆኑ የተለያዩ የሃይማኖት ተቋማት የሚዲያ ተወካዮች አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡



ፎቶ፡ በናኦል አየለ

# ኮምቦልቻ ኢንዱስትሪ ፓርክ በአሸባሪው ሕወሓት ወረራ ከግማሽ ቢሊዮን ብር በላይ አጠቃላይ ጉዳት እንደደረሰበት አስታወቀ

**- ፓርኩ በ2014 በጀት ዓመት ከሰባት ነጥብ አራት ሚሊየን ዶላር በላይ የውጭ ምንዛሪ አግኝቷል**

**ፋንታነሽ ክንዴ**

ኮምቦልቻ፡- እስካሁን በተደረገ ጥናት በአሸባሪው የሕወሓት ቡድን ወረራ ከግማሽ ቢሊዮን ብር በላይ አጠቃላይ ውድመት እንደደረሰበት የኮምቦልቻ ኢንዱስትሪ ፓርክ አስታወቀ። ፓርኩ በ2014 በጀት ዓመት ከሰባት ነጥብ አራት ሚሊዮን ዶላር በላይ የውጭ ምንዛሪ ማግኘቱም ተገለጸ።

የኮምቦልቻ ኢንዱስትሪ ፓርክ ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ አሕመድ ሰኢድ በፓርኩ ጉብኝት ላደረጉ ጋዜጠኞች እንደገለጹት፤ እስካሁን በተደረገ ጥናት ፓርኩ በአሸባሪው ሕወሓት ወረራ ምክንያት ከግማሽ ቢሊዮን ብር በላይ አጠቃላይ ጉዳት ደርሶበታል። ጥናቱ ገና ስላልተጠናቀቀ የደረሰው ጉዳት ከዚህም ከፍ ሊል እንደሚችል ጠቁመዋል። ከባለፈው ሐምሌ ወር ጀምሮ ሰባት ነጥብ ሰባት ሚሊየን ዶላር የሚያወጡ ምርቶችን ወደ ውጭ ለመላክ አቅዶ ከሰባት ነጥብ አራት ሚሊየን ዶላር በላይ የውጭ ምንዛሪ ማግኘቱን ያስታወቁት አቶ አህመድ፤ ከተገኘው አጠቃላይ የውጭ ምንዛሪ ውስጥ ሶስት ነጥብ አራት ሚሊዮን ዶላሩ ፓርኩ በመልሶ ማቋቋም ወደ ሥራ ከተመለሰ በኋላ የተገኘ መሆኑን አስረድተዋል። በአሸባሪው ቡድን ከፍተኛ ውድመት የደረሰበት የኮምቦልቻ ኢንዱስትሪ ፓርክ ከጦርነቱ በፊት ሶስት ሺ 200 ሠራተኞች እንደነበሩት ገልጸው፤ ድጋሚ ሥራ ሲጀምር ወደ ሥራ የተመለሱት ወደ ሁለት ሺ አንድ መቶ የሚጠጉ ሠራተኞች ብቻ ናቸው። ቀሪ ሠራተኞችን ወደ ሥራ ለመመለስም ከካምፓኒዎች ጋር በመሆን ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን ገልጸዋል። ኮምቦልቻ ኢንዱስትሪ ፓርክ ከጦርነቱ በኋላ ወደ ሥራ ሲመለስ ካምፓኒዎች ሠራተኞችን እንዲመልሱና በጦርነቱ ምክንያት ሳይከፈላቸው የቆየውን ደመወዝ እንዲከፍሉ ለማድረግ ሥራዎች መሠራታቸውን የጠቆሙት ሥራ አስኪያጁ፤ ካምፓኒዎችን ለማገዝም የሰባት ወራት የሼድ ኪራይ እፎይታ መሰጠቱን ተናግረዋል። ኮምቦልቻ ኢንዱስትሪ ፓርክ በአጠቃላይ አስር ሼዶች እንዳሉት የተገለጸ ሲሆን፤ ከዚህ ውስጥ ዘጠኙ ለባለሀብቶች መተላለፋቸውን ከፓርኩ ያገኘነው መረጃ ያመለክታል።

# ‹‹የክልሉን ሕዝብ ተጠቃሚነት ማጎልበት የሚችሉ ተግባራት በትኩረት እየተከናወነ ይገኛል››

**- የሐረሪ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ኦርዲን በድሪ**

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የሐረሪ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ኦርዲን በድሪ ለክልሉ ምክር ቤት ጉባኤ ባቀረቡት የስድስት ወር እቅድ አፈጻጸም ሪፖርት የክልሉን ገቢ ለማሻሻል በተከናወኑ አዳዲስ የአሠራር ሥርዓት በግማሽ ዓመቱ ከ580 ሚሊዮን ብር በላይ ገቢ መሰብሰቡን ገልጸዋል።በማኅበራዊ ዘርፍ በትምህርትና ጤና ዘርፎች ተደራሽነትንና ጥራትን ማረጋገጥ የሚያስችሉ ተግባራት ተከናውነዋል ብለዋል፡፡

በግማሽ ዓመቱ ለ6ሺህ 173 ዜጎች የሥራ እድል ለመፍጠር ታቅዶ ለ4ሺህ 988 ዜጎች የሥራ እድል መፍጠር መቻሉን ጠቅሰው፤ ከ27 ሚሊዮን ብር በላይ ብድር መሰራጨቱን ነው በሪፖርቱ የጠቆሙት፡፡

የቱሪዝም ምርቶችን በማልማትና በማስተዋወቅ በተከናወነ ተግባርም በግማሽ ዓመቱ 60 ሺህ የአገር ውስጥ እንዲሁም 447 የውጭ ዜጎች ክልሉን መጎብኘታቸውን የጠቆመት ርዕሰ መስተዳድሩ አፈፃፀሙ ከአምናው ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀርም የመቶ ፐርሰንት ጭማሪ አሳይቷል ብለዋል፡፡

የኑሮ ውድነትን ከመከላከልና ከመቀነስ ጋር ተያይዞም በክልሉ ባለፉት 6 ወራት ከ508 ሺህ ሊትር በላይ የምግብ ዘይት እና ሌሎች መሠረታዊ የምግብ ሸቀጦች በተመጣጣኝ ዋጋ መሰራጨቱን እንዲሁም የዋጋ ግሽበት እንዲባባስ በሚያደርጉ አካላት ላይ ቁጥጥር የማድረግና የአቅርቦት ችግርን ለመቅረፍ በትኩረት ሲሠራ መቆየቱን አመላክተዋል፡፡

በግብርና ዘርፍ በግማሽ ዓመቱ 224 ሺህ 375 ኩንታል ምርት የተሰበሰበ ቢሆንም ከአምናው ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር የ23 በመቶ ቅናሽ ማሳየቱንና ለዚህም በምርት ዘመኑ ወቅቱን የጠበቀ ዝናብ ባለመዝነቡ ምክንያት መሆኑን አንስተዋል፡፡



በክልሉ ገጠርን ከከተማ የሚያገናኙ 45 ኪሎሜትር የመንገድ ፕሮጀክቶችን ጨምሮ የተለያዩ ፕሮጀክቶችን ተግባራዊ ለማድረግ ሲሠራ መቆየቱን ጠቁመው ሆኖም ግን የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች በአግባቡ ባለመከናወናቸው፤ ሥራዎችን በወቅቱ አለመጀመር እንዲሁም በዋጋ ንረት ተፅዕኖ ምክንያት የካፒታል ፕሮጀክቶች አፈፃፀም በሚፈለገው መልኩ እንዳይሆን አድርጓል ብለዋል፡፡

ሕገወጥ የመሬት ወረራንና ሕገወጥ ግንባታን ለመከላከል የክልሉ ሰላም ለማረጋገጥ ርብርብ እየተደረገ መሆኑንም አንስተዋል ርዕሰ መስተዳደሩ፡፡

በቀጣይም የታዩ ውስንነቶችን በመቅረፍ የአርሶ አደሩን ምርትና ምርታማነትን ለማጎልበት፣ የኑሮ ውድነትን ለማረጋጋት፣ በከተማና ገጠር ለሚገኙ ወጣቶች ተጠቃሚነትን ሊያጎለብቱ በሚችሉ ተግባራት፣ በብድር አመላለስ ጋር ተያይዞ ያሉ ችግሮችን ለመቅረፍ በቁርጠኝነት ይሰራል ብለዋል፡፡

ሕገወጥ የመሬት ወረራን ለመከላከል፣ የክልሉን ሰላም ለማረጋገጥ፣ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ለመቅረፍ እና የሕዝቡን መሠረታዊ ችግሮች ሊቀርፉ የሚችሉ ተግባራት ለማከናወን በታላቅ ወኔና ተነሳሽነት እንደሚሠራ መናገራቸውን የክልሉ መንግሥት ኮሙዩኒኬሽን አስታውቋል።



አቶ ግዛቸው ሙሉነህ

# የተፈናቃዮችና የተረጂዎች ቁጥር መጨመር እንዳሳሰበው የአማራ ክልል ገለጸ

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- የተፈናቃዮች እና የተረጂዎች ቁጥር ከ11 ነጥብ ስድስት ሚሊዮን በላይ መድረሱና በየጊዜውም መጨመሩ አሳሳቢ መሆኑን የክልሉ ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ ኃላፊ አቶ ግዛቸው ሙሉነህ ገለጹ፡፡

አቶ ግዛቸው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የተፈናቃዮችና የተረጂዎች ቁጥር መጨመር አሳሳቢ ነው። የሕወሓት ኃይል ወረራ በፈጸመባቸው አጋጣሚዎች አጠቃላይ ከአካባቢያቸው ተፈናቀሉ ዜጎች ከ11 ነጥብ ስድስት ሚሊዮን በላይ አሻቅቧል፡፡ በየጊዜውም የተፈናቃዮችና የተረጂዎች ቁጥር እየጨመረ ይገኛል፡፡

ከዚህ ቁጥር ውስጥ ዘጠኝ ነጥብ ሶስት ሚሊዮን በጦርነቱ ጊዜ አካባቢያቸው በወረራ ላይ የነበረ፣ ሃብት ንብረታቸውን የተዘረፉ፣ በወቅቱ ማምረት ያልቻሉና ከንግድ ሥርዓት ውጭ ሆነው በመቆየታቸው ወደ ቀዬአቸው ቢመለሱም መሠረታዊ የርዳታ ድጋፍና ሕክምና የሚፈልጉ ናቸው፡፡

ቀሪዎቹ ደግሞ ከዘመድ የተጠጉ፣ በካምፕ የሚኖሩ እና ድጋፍ የሚፈልጉ ናቸው፤ተረጂዎቹ የዕለት ምግብ፣ አልባሳት፣ የምግብ እጥረት፣ የሕክምና እና የቁሳቁስ ችግርም እንዳለባቸው አመልክተዋል፡፡

የተፈናቃይ ቁጥር ለመጨመሩ ምክንያቱ አሁንም በሕወሓት ኃይል ወረራ ውስጥ ያሉ የአማራ አካባቢዎች መኖራቸው ነው ያሉት አቶ ግዛቸው፤ አላማጣና አካባቢው፣ ኮረምና አካባቢው ዋግ ላይ ሁለት ወረዳና በሶስተኛ ወረዳ ደግሞ ስድስት ቀበሌዎች በአሸባሪው ሕወሓት ኃይል በወረራ ላይ ይገኛሉ ነው ያሉት፡፡

እንደርሳቸው ማብራሪያ፤ በተመሳሳይ በሰሜኑ ክፍልም ነጻ ያልሆኑ የማይጠብሪና አዲአርቃይና አካባቢዎች በጠላት ኃይል ስር ናቸው፡፡ ጠላት መንገዱን በሙሉ በመዝጋቱ ለእነዚህ ሰዎች ርዳታ ለማቅረብ አስቸጋሪ ሆኖብናል፡፡ ርዳታ ለሚፈልግ የትግራይ ሕዝብና ለአማራ ክልል ነዋሪዎችም ርዳታ እንዳይደርስ መንገዱን ዘግቷል፡፡

በአካባቢው የሚኖሩ ሰዎች ረሃብ ስለገጠማቸው እየሾለኩ ወደ አዋሳኝ ነጻ ቦታዎች እየገቡ ናቸው። በተያዘው ሳምንት ከዋግ ብቻ የተፈናቀሉ 65 ሺህ ደርሰዋል፣ ረሃብን ሸሽተው የሚገቡ የትግራይ ተወላጆችም አሉ፡፡ መንግሥት ለእነዚህ ሰዎች ሰብዓዊ ርዳታ ማቅረብ አለበት፡፡

እነዚህ ተፈናቃዮች ከአንድ ነጥብ ሶስት ሚሊዮን ኩንታል በላይ እህል ያስፈልጋቸዋል፡፡ በመሆኑም እነዚህን ሰዎች ለመመገብ ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብ ያስፈልጋል ያሉት አቶ ግዛቸው፤ የተሟላ የሰብዓዊ ድጋፍም ለማድረግ ጥረት እየተደረገ ይገኛል ብለዋል፡፡

70 በመቶ በመንግስት ቀሪውን የአካባቢው ባለሃብቶች፣ ረጂ ድርጅቶችን በማስተባበር አስፈላጊው ድጋፍ እየቀረበ ቢሆንም፤ በሚፈለገው ልክና የተሟላ ድጋፍ እየተደረገ አይደለም፣ አልፎ አልፎ መዘግየቶች አሉ፡፡

አሁንም ዜጎችን የማፈናቀል ሥራ እየሠሩ የሚገኙ አካላት አሉ፡፡ ማኅበረሰቡ ከኀብረተሰቡና ከአጎራባች ክልሎች ጋር በመቀናጀት ድርጊቶቹን ማስከንና ሕዝቡን ወደልማት ማስገባት ካልተቻለ የሚፈናቀልና የሚገደል ሕዝብ ቁጥር ማሻቀቡ አይቀርም፡፡

የሕወሓት ኃይልም እልባት ካላገኘ ችግሩን ለማባባስ መጣሩ አይቀሬ ነው፡፡ አደጋውን ተረድቶ እንደመንግሥት መሥራት ትኩረት ሊሰጠው ይገባል ብለዋል፡፡

ገዢው መንግሥት ጉባኤ ካካሄደ በኋላ ከሕዝብ ጋር ባካሄደው ውይይት የሰላም ጉዳይ አሳሳቢ መሆኑ ተነስቷል፡፡ ሰላም ለማስፈን መፍትሔዎችና አቅጣጫዎችም ተቀምጠዋል፡፡ ሕዝቡን የሰላሙ ባለቤት የማድረግና ሥራ ዕድል ፈጠራ ላይ ማተኮር የመፍትሔዎቹ አካል ናቸው ብለዋል፡፡

ዜና

በኢፌዴሪ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት
FDRE Government Communication Service

# በአፋር ክልል በአብኣላ በኩል እርዳታ ወደ ትግራይ ክልል መጓጓዝ ጀመረ

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፤ በዓለም ምግብ ድርጅት አማካይነት 21 ከባድ የጭነት መኪናዎች የእርዳታ እህል በመጫን በአፋር ክልል በአብኣላ በኩል የሰብዓዊ እርዳታ በየብስ ትራንስፖርት ወደ ትግራይ ክልል ማጓጓዝ መጀመሩን የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት አስታወቀ።

የኢትዮጵያ መንግሥት በትግራይ ክልል ውስጥ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ያሉ ዜጎችን ሕይወት ለመታደግ ሁሉንም አማራጮች በመጠቀም የሰብዓዊ እርዳታን ለማቅረብ እንቅስቃሴ መጀመሩ የሚታወስ ነው፡፡

ውሳኔው ከተወሰነበት ቀን ጀምሮ የመድኃኒት፣ የሕክምና መሣሪያዎች፣ ገንዘብና አልሚ ምግቦችን ረጂ ድርጅቶች በቻሉት መጠን በአየር ትራንስፖርት በየዕለቱ ማጓጓዝ መጀመራቸውን የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ለፋና ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት በላከው መግለጫ አመላክቷል፡፡

በዛሬው ዕለትም በዓለም ምግብ ድርጅት አማካይነት 21 ከባድ የጭነት መኪናዎች የእርዳታ እህል በመጫን በአፋር ክልል በአብኣላ በኩል የሰብዓዊ እርዳታ በየብስ ትራንስፖርት ወደ ትግራይ ክልል ማጓጓዝ መጀመራቸውን ነው ያስታወቀው።

የኢትዮጵያ መንግሥት የሰብዓዊ እርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ዜጎች የሰብዓዊ ድጋፍ አቅርቦቱን በተሟላ ሁኔታ ለማስኬድ ከተባባሪና ባለድርሻ አካላት ጋር ለመሥራት ዛሬም ቁርጠኛ መሆኑንም አጽንኦት ሰጥቷል፡፡

# ‹‹ምክክሩ በመቃብራችን ላይ ይባሉ የነበሩ አጀንዳዎች ለውይይት የሚቀርቡበት በመሆኑ ከምንም በላይ አስፈላጊ ነው››

-አቶ የሽዋስ አሰፋ
የኢዜማ ሊቀመንበር

አዲሱ ገረመው



አዲስ አበባ፡- አገራዊ ምክክሩ ከዚህ በፊት በመቃብራችን ላይ ይባሉ የነበሩ አጀንዳዎች ለውይይት የሚቀርቡበት መድረክ በመሆኑ ከምንም በላይ አስፈላጊ ነው ሲሉ የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትሕ (ኢዜማ) ሊቀመንበር አቶ የሽዋስ አሰፋ ገለጹ፡፡

አቶ የሽዋስ የአገራዊ ምክክሩን አስፈላጊነት አስመልክቶ ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር ባደረጉት ቆይታ፤ ከዚህ በፊት የባልና ሚስት ጸብ አይደለም እየተባለ ይናቅ የነበረ ጉዳይ አሁን ላይ አስፈላጊ መሆኑ ታምኖበት፣ በጀት ተመድቦና ኮሚሽን ተዋቅሮ እየተሠራ መሆኑ መልካም ጅምር ነው ብለዋል፡፡ ምክክሩ ከዚህ በፊት በመቃብራችን ላይ ይባሉ የነበሩ አጀንዳዎች ለውይይት የሚቀርቡበት እንደመሆኑ ትልቅ ጥቅም እንዳለውም ገልጸዋል፡፡

አገራዊ ምክክሩ ከምርጫና መሰል ተግባራት በላይ ትልቅ መሆኑን የገለጹት አቶ የሽዋስ፤ በኢዜማ በኩል ይሄንን የሚከታተልና ሰነዶችን የሚያዘጋጅ ቡድን መቋቋሙን፤ ኮሚሽኑ ጥሪ በሚያደርግበት ጊዜ እንደ ፓርቲ ያላቸውን አቋም፣ አጀንዳና እምነት እንደሚያቀርቡም ጠቅሰዋል፡፡

ምክክሩ ጭቅጭቅ ውስጥ የማይገባበት፤ እንደ ሰንደቅ ዓላማ፣ ሕገ መንግሥትና የፌዴራል አወቃቀር ያሉ ጉዳዮች፤ እንዲሁም አንድ አገር አሉኝ የምትላቸው ምልክቶች፣ ብሔራዊ ጀግኖች፣ ታሪክና ረጅም ጊዜ ሲንከባለሉ የመጡ አጀንዳዎች የሚዘገቡት መሆን እንዳለበትም አቶ የሽዋስ ገልጸዋል፡፡ መንግሥት ኮሚሽኑን የማገዝ ትልቅ ኃላፊነት እንዳለበትና ከአሠራሩ ደግሞ እጁን ማራቅ እንደሚገባውም ተናግረዋል፡፡

ምክክሩ የሚመለከተው ፓርቲን ብቻ እንዳልሆነ፤ ፓርቲ ለምክክሩ አንድ አካል እንጂ ብሔራዊ ምክክሩ የአገርና የሕዝብ ፕሮጀክት መሆኑን ጠቁመዋል፡፡ በዚህ ውስጥ እንደ አንድ መልካም አሳቢ ፖለቲከኛና ኃላፊነት እንደሚሰማው የፖለቲካ ድርጅት አጀንዳዎቹም ላይ ሆነ ሂደቱ ላይ እንዲሁም አፈጻጸሙ ላይ የራሳቸውን መልካም አስተዋጽኦ እንደሚያደርጉ አመላክተዋል፡፡

ለምክክሩ ፖለቲካ ፓርቲዎች አንድ ባለ ድርሻ እንጂ ብቸኛ አካል ባለመሆናቸው፤ የፖለቲካ ኤሊቱና መንግሥትን ጨምሮ ሁሉም ለሕዝቡ ውሳኔ ተገዢ መሆን እንዳለባቸው፤ ከምክክሩ በኋላ ለምርጫ የሚደረገው ውይይትና ክርክርም ፖሊሲዎች ላይ ያተኮረ እንጂ ከአሁን ቀደም ሲያጨቃጭቁ በነበሩ ጉዳዮች ላይ መሆን እንደሌለበትም ጠቅሰዋል፡፡ “ሕዝብ የሚያመጣውን ዋና ዋና ጉዳዮች ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ዘግተን ወደ ፊት እንሄዳለን የሚል ተስፋ አለኝ” ሲሉ ተናግረዋል፡፡

እስካሁን ከተደረጉ ሂደቶች መካከል አዋጅ ማጽደቁ ላይ ጉድለቶች ቢኖሩበትም መልካም ነገር እንደሆነ አቶ የሽዋስ ጠቅሰዋል፡፡ የኮሚሽነሮቹን መሾም በተመለከተም ኢዜማ በተሿሚዎቹ ላይ ችግር የለም ብሎ እንደሚያምን ሂደቱ ላይ ግን ቅሬታ እንደነበረውም አስታውሰዋል። ሆኖም ፕሮጀክቱን ለአገር በሚጠቅም መልኩ እያገዙ መሄድ አስፈላጊ መሆኑን ፓርቲያቸው ያምናል ነው ያሉት፡፡

## ‹‹ፖለቲካዊ መፍትሔ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ውስጥ ለዋነኛ ችግሮች መፍትሔ ለመስጠት ትክክለኛው እርምጃ ነው፡፡

አገራዊ ምክክር ለማካሄድ የሚያስችል ተቋም ለመመሥረት በመንግሥት በኩል ቁርጠኝነት ታይቷል፤ ኮሚሽኑ በተገቢው ሥራውን እንዲሠራ በቀጣይም እገዛና ድጋፍ ማድረግ ከሁሉም አካል ይጠበቃል ብለዋል፡፡ ኢትዮጵያ የሚያስፈልጋት ዘርፍ ብዙ ለውጥ በመሆኑ በፖለቲካና በዲሞክራሲ ብቻ ሳይሆን በኢኮኖሚ፣ በትምህርት፣ በቴክኖሎጂ፣ በባህልና በሌሎች ዘርፎች ጭምር ነው ሲሉ ተናግረዋል፡፡

እንደ ኮሚሽኑ ገለጻ፤ አገራዊ ምክክሩ ውጤታማ እንዲሆንም የሌሎች አገሮችን ተሞክሮ ማየት ያስፈልጋል፡፡ ከኛ ማንነት ጋር አዛምዶ መፍትሔ መስጠትን ይጠይቃል። ኮሚሽነሮች ሥራቸውን መሥራት እንዲጀምሩ እድልና ድጋፍ መስጠት እንጂ ከተመሠረተ ወራቶችን ያላሳለፈ ኮሚሽንን መተቸት አስፈላጊ አለመሆኑን አስረድተዋል፡፡

የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን በብዙ ዘርፎች ከአገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ ጋር የሥራ ግንኙነት ይኖረዋል ያሉት ኮሚሽነሩ፤ በፖለቲካ ቀውስ ሳቢያ በአገራችን ካሉ ችግሮች ውስጥ አንዱ የሰብዓዊ መብት ቀውስ በመሆኑ አገራዊ ምክክሩ የሰብዓዊ መብቶች መርሕ ላይ ተመሥርቶ እንዲካሄድ የምናደርገው ክትትል ይኖራል። እንዲሁም በዘላቂነት ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል የምንላቸውን ጭብጦች የኮሚሽኑ ትኩረት እንዲሆኑ እናደርጋለን ብለዋል፡፡

እንደ ዶክተር ዳንኤል ገለጻ፤ ኮሚሽናኖች ከሚያከናውኑት ተግባር ውስጥ ለአገራዊ ምክክሩ አስፈላጊ የሆኑ ጭብጦችን መርጦ ማውጣት በመሆኑ በዚህ ሂደት ውስጥም ኢሰመኮ ሚና ይኖረዋል፡፡ የሚመረጡት ጭብጦች ወይም ርዕሰ ጉዳዮች ላሉብን ችግሮች መፍትሔ የሚሰጡ እንዲሆኑ ጭብጦችን በመለየት፣ ውይይቱ ሰብዓዊ መብትን ባከበረ መልኩ እንዲከናወን ለማድረግና ከአገራዊ ምክክር ኮሚሽነሮች የሚወጡ ምክረ ሀሳቦችን የሰብዓዊ መብት መርሆችንና ግዴታዎችን ያከበሩ መሆናቸውን እናረጋግጣለን፡፡ ምክክር በመስጠትና የሙያ ድጋፍ በማድረግ ከኮሚሽኑ ጋር ተቀራርበን እንሠራለን ብለዋል፡፡

## የኢትዮጵያ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ተዘግቷል፡፡ በተለያዩ አካባቢዎች ተሰድደው የሚገኙና የተቸገሩ ወገኖችን ልናግዛቸው ይገባል፡፡

በአፋርና በወሎ ለተፈናቀሉ ወገኖች መንግሥት እና ባለሃብቱ ርዳታ አድርገዋል ያሉት ተቀዳሚ ሙፍቲ ሐጂ ኡመር ኢድሪስ፤ በወለጋ ያሉ ወገኖች ድጋፍ አላገኙም፣ በለቅሶና በኃዘን በአስቸጋሪ ሁኔታ ላይ በመሆናቸው ልንደግፋቸው ይገባል ብለዋል፡፡

በአፋር፣ በሶማሌ እና በኦሮሚያ ክልሎች ድርቅ መከሰቱን በማስታወስም፤ ከብቶች አልቀዋል ሙስሊም ክርስቲያን እየተቸገሩ ይገኛሉ፡፡ ከጦርነቱም ከበሽታውም ድርቅ የከፋ መሆኑን በ1977 ዓ.ም በተከሰተበት ወቅት አይተነዋል፤ አስቸጋሪ ነበር ድርቁን አላህ እንዲያነሳልን በረመዳናችን ወቅት መጸለይ ያስፈልጋል፡፡

ፈጣሪ ገንዘብ የሰጣችሁ ወንድሞችና እህቶች እነዚህን ወገኖች መደገፍ ውዴታ ሳይሆን ግዴታችሁ ነው፡፡ ገንዘብ ያላችሁ ሰዎች ያለቦታውና ያላግባብ፣ ካለመጠን ገንዘብ ካወጣችሁ እንደ አባካኝነት ትቆጠራላችሁ፤ ማባከን ሃራም በመሆኑ ልትጠነቀቁ ይገባል፡፡ በረመዷን ጾም ወቅት ድሆችን ማገዝ፣ የቸገራቸውን መደገፍ፣ የከፋቸውንና ያዘኑትን ማጽናናት እና ከጎናቸው በመሆን መተባበር አለባቸው ሲሉም መክረዋል፡፡

በሳዑዲ የታሰሩ ወገኖችን በመንግሥት አማካኝነት ሄደው መመልከታቸውን በመጠቆምም፤ አሁን እየተመለሱ መሆኑ ያስደስታል፣ ለዚህም ለፈጣሪ ታላቅ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡

የቀሩ ወገኖችም እንዲመለሱ መደረግ አለበት፣ የተመለሱትም በአገራቸው ላይ ለፍተው መኖር እንዲችሉ መነሳሳት እንዳለባቸው እና አስፈላጊ ድጋፍም ሊደረግላቸው እንደሚገባ ተቀዳሚ ሙፍቲ ሐጂ ኡመር አሳስበዋል፡፡

ከባርነት ነጻነት ይሻላል፣ የሰው አገር ኑሮ ባርነት እና አሽከርነት ነው፡፡ በባርነት ከመኖር ይልቅ የነጻነት አየር እየተነፈሱ አገር ላይ መኖርና ሠርቶ መለወጥ ይገባልም ብለዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በውጭ አገር የሚገኙ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ሕዝበ ሙስሊም ወደ አገራቸው ገብተው በዓሉን እንዲያከብሩ እና እንዲደሰቱ ያስተላለፉት ጥሪ የሚያቀራርብ እና የሚያስተዋውቅ ነው፡፡ ረመዳንን ለማክበር የሚመጡ ወንድሞቻችንንና እህቶቻችንን ለመቀበል እየተዘጋጀን እንገኛለን ሲሉም ገልጸዋል፡፡

ወንድም ካሊድ ምግባረ ሰናይ ፋውንዴሽን ከኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ጋር በመሆን በችግር ላይ ላሉና ማፍጠሪያ ለሌላቸው ወገኖች እንዲሁም ለሁሉም ስደተኞች እንዲደርስ ታሳቢ ያደረገ ለአንድ ወር የሚቆይ የርዳታ ማሰባሰቢያ መርሐ ግብር እንደሚያከናውን ጠቁመዋል፡፡

በተለይ ከወለጋ የሚመጡ ወገኖች አጣዳፊ ድጋፍ ይፈልጋሉና እንድትደግፉ አደራ እላለሁ ብለዋል፡፡ ድጋፉን የሚያሰባስብ ኮሚቴ እንደሚቋቋምም አመልክተዋል፡፡ ድጋፉ የሚሰበሰብበት ስፍራ ምክር ቤቱ አፍሪካ ሕብረት አጠገብ በተረከበው ስፍራ እንደሚሆንም ተጠቁሟል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## ሕዝቦችን በማጋጨት አገር የማፍረስ ሴራ መቼም አይሳካም!

በአገራችን በተለይ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ሕዝቡን በተለያየ መልኩ በማጋጨት የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት ቀን ከሌሊት ሳይታክቱ የሚሠሩ ሴረኞች በርክተዋል።

ለዚህም መጠቀሚያ የሚያደርጉት አንዱን ብሔር በሌላው ላይ ማነሳሳት ነው። በአንዱ ብሔር ላይ ጥቃት በመፈጸምና ይህንኑ በሚዲያዎቻቸውና በማህበራዊ ድረገጾች ጭምር በማራገብ የሚገለጽ ነው። ወይም ደግሞ አንዱን ሃይማኖት በሌላው ላይ ሊያነሳሳ የሚችል ጥቃት በመሰንዘር፤ የኃሳ መሪዎችን በመግደል የሕዝቡን ስስ ብልት በመፈለግና እሱን ወደፊት አውጥቶ በማጋጋል የሚገለጽ ነው። ይሄ የሕዝቦች ዘላቂ አብሮነትና ሁለንተናዊ ብልጽግና ጉዞን ለማደናቀፍ የተወጠነ የጥፋት ዕቅድ አካል መሆኑ ግልጽ ነው። የዚህ ሁሉ ሴራ ማጠንጠኛው ደግሞ ሕዝብን አጋጭቶና አለያይቶ አገር ማፍረስ ነው።

ይሁን እንጂ ሕዝብን በማጋጨት አንድነቱን በማናጋት አገር ማፍረስ የተነቃበት የሴራ ዓይነት ነው። ሆኖም አሁንም ሴራው ቀጥሏል። እነጭር ሲል አንወድም ገና ከመነሻው የተሰናከለ ሀሳባቸው ቢሳካም ባይሳካም የሴራ ፖለቲካቸውን ወደፊትም እንደሚቀጥሉበት ይታመናል። አንዱ መንገድ ሲዘጋባቸው ሌላ እየከፈቱ፤ የቆፈሩት ጉድጓድ ሲደፈን ሌላ እየሸነቆሩ ይቀጥላሉ። አሁን አብዛኛው ማህበረሰብ የሴራ ፖለቲካውን እያወቀ እና እየተረዳ መጥቷል።

እንደሚታወቀው አሸባሪው ሕወሓት የትግራይን ሕዝብ ከአማራው ወንድምና እህቱ ለመለያየት ያልቆፈረው ጉድጓድ፤ ግጭቱን ሕዝባዊ ለማድረግ ያልፈጸመው ጥቃት አልነበረም። ይሄ ለእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው። ያ ሁሉ በጭካኔና አረመኔነት የተሞላው ሴራ በሁለቱ ብሔረሰቦች መካከል የነበረውን የኖረ ግንኙነት በማፍረስ ቂምና ቁርሾን በማሳደግ ሕዝቡን ለመለያየት ነበር።

ይሁንና አሁን እንደታየው ግን ሕዝቡ አልተለያየም። ዛሬም የትግራይ ሕዝብ ሲርበውና ሲቸግረው የተሰደደው ወደ አማራው ወገኑ ነው። ‹‹አይዞህ ያለንን ተካፍለን ይሄን ክፉ ዘመን አብረን እናሳልፋለን›› ብሎ የተቀበለውም አማራ ወገኑ ነው።

የአማራውን ሕዝብ ከወንድም የኦሮሞ ሕዝብ ደም ለማቃባት እጅግ አስከፊ ድርጊቶች ተፈጽመዋል። አማራና ኦሮሞ ነገ ወገኔ እንዳይባባሉ ሊያደርግ የሚያስችል ግፍ ተፈጽሟል። በትግራይና በአፋር፤ በኦሮሚያና በሱማሌ፤ በአማራና በቤኒሻንጉል ጉሙዝ እንዲሁም በሌሎችም አጎራባች አካባቢዎች ሁሉ ብሔርን ከብሔር የማጋጨት በዚህ መሀል በሚገኝ ትርፍ አገርን ለማፍረስ ጥረት ተደርጓል። በርግጥ በዚህ መካከል በርካቶች ተጎድተዋል። ሕይወት ጠፍቷል፤ ንብረት ወድሟል። ሆኖም ባሰቡት ሴራ ልክ አገር ማፍረስ የማይቻል፤ ዕቅዱም የቁም ቅዠት መሆኑን አይተውታል።

ዛሬም ‹‹ካፈርኩ አይመልሰኝ እንዳለው ሌባ›› የግጭት አትራፊዎች ከለመዱት ጥፋታቸው አልተማሩም። ሕዝብን ከሕዝብ ጋር በማጋጨት ግጭቱን የብሔር ወይም የሃይማኖት እንዲመስል ከመሥራት አልቦዘኑም። የግጭት ጥንስሳቸውን መልኩንና አካባቢውን በመቀያየር ከመደፍደፍ አልተለዩም። ሕዝብን ከማደናበርና ከማስጨነቅ አልተቆጠቡም። በመሆኑን ሕዝቡ አሁንም በየቦታው የሚሰማው የሽብር ተግባር የጽንፈኞች ሴራ መሆኑን በውል ሊገነዘበው ይገባል።

ሕዝብ ከሕዝብ ጋር ጸብ የለውም። ሕዝብ እንደ ሕዝብ አይጋጭም፣ አይጣላም፣ በቂምና ቁርሾም አይጫረስም። ነገር ግን ግጭቱን ለመቀስቀስ ብሎም ለማባባስ የሚሠሩ እንዳሉ ልብ ማለት ይገባል። ረጋ፣ ሰከን ብሎ ማሰብ ይጠይቃል። የጥቃቱ ተዋናይም ሆነ ተጠቂ ከመሆን መጠንቀቅ ያስፈልጋል። መንግሥት ለአገርና ለሕዝብ ብሎ በሚወስዳቸው የሰላምና የጸጥታ ጉዳዮች ላይ መተባበር ይገባል። አካባቢን ነቅቶ መጠበቅ ያስፈልጋል።

በየጊዜው ከተፈጠረው ግጭት፣ ከጠፋው የሰው ሕይወትና ከወደመው ንብረት በላይ የተራገበው ፕሮፓጋንዳ ገዝፎ ይገኛል። ይሄ ርካሽ የፖለቲካ ትርፍ ለማግኛ ነው። ከድርጊቱ በላይ በፕሮፓጋንዳ ጉዳዩን በማራገብና በማክበድ የእርስ በእርስ ግጭቶች እንዲስፋፉ አንዱ ብሔር በሌላው ላይ በባላንጣነት እንዲነሳሳ የሚደረግ ትንኮሳ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል።

በማንም አጀንዳ የሚፈርስ አገር፣ የሚበተን ሕዝብ የሚጋጭና ደም የሚቃባ ብሔር እንደሌለ እንደከዚህ ቀደሙ ሁሉ ነገሮችን በትዕግስትና በሰከነ መልኩ ተረድቶ ሴረኞችን ማሳፈር ያስፈልጋል።

የኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያ አንድነት ዕረፍት የነሳቸው ጽንፈኞች ለማይሳካ ሕልማቸው ሕዝብን እረፍት በመንሳት፣ አገር እንዳትረጋጋ ማድረግ ተገቢ አይደለም። አሁንም ወደፊትም ሕዝብን በማናከስ አገርን ለማፍረስ የሚሸረበው ደባ አይሳካምና እጃችሁን ሰብስቡ። ሕዝቡም ጉዳዩ አገር ለማፍረስ በተደጋጋሚ ጊዜ የሚሸረብ ተንኮል መሆኑን ተገንዝቦ በቃ ሊላቸው ይገባል!


ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ
- ዘላለም ግርማ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

## «ሕዝቡ ምን ይላል? ...ሕዝቡማ ... !!!»

**ከአስባቸው ደሳለኝ አበሻ (ለንደን)**

እንደምን አላችሁልኝ ውድ የአዲስ ዘመን ጋዜጣ አንባቢዎች!! እንደተለመደው በዛሬው መጣጥፌ አንድ ሀሳብ ልሰንዝርና እናንተም በነፃው ሀሳብ አምድ ላይ ተወያዩበት:: ልክ እንደ ተፈጥሮ ሁሉ ሕዝቦችም ከተፈጥሮና ከታሪክ የሚመነጭ አንድነትና ልዩነት አላቸው:: ሕዝቦች ሁሉ በሕዝብነታቸው አንድ ናቸው::

በእርግጥ አንድ ሕዝብ ከሌላው ሕዝብ በተፈጥሮውና በቆዳ ቀለሙ በታሪክ ሂደት ውስጥ በተፈጠረው ዳር ድንበር፣ ባሕል፣ ቋንቋ፣ እምነት፣ ሥነ ልቦናዊ አመለካከት ኢኮኖሚያዊ እድገት ቢለያዩም ሕዝብን ሕዝብ የሚያሰኙ የወል ባሕሪያቶችን ይጋራሉ:: ስለዚህ ሕዝቦች በአንድነታቸው ውስጥ ልዩነት በልዩነታቸው ውስጥ አንድነት አላቸው:: በመሆኑም በዛሬው ዓለም ትልቁ የሕዝቦች መታወቂያ አገር ነው:: መታወቂያቸው ከሁሉም በላይ ስለሆነ ከራሳቸው ይልቅ፣ ብዙዎቹ አገራቸውን ይወዳሉ::

በአንድ በኩል አንድነት በሌላ በኩል ደግሞ ልዩነት መኖሩ ይታወቃል:: እኛ ኢትዮጵያውያን ደግሞ የምንኖርባት አፍሪቃ ከምድር ጠቅላላ ስፋት ስድስት በመቶውን፤ ከመሬቷ ደግሞ ወደ ሃያ ተኩል በመቶውን የምትሸፍን በመሆኑ፣ በገጸ ምድር ስፋትና በሕዝብ ቁጥር ከእስያ ቀጥላ ሁለተኛ መደብን የያዘች አህጉር ነች። በአሰፋፈራችን ደግሞ በአፍሪካ ቀንድ የምንገኝ የረጅም ዘመን ታሪክ ባለቤት አገር ያለን በመሆናችን ነፃነታችንን ጠብቀን የኖርን ሕዝቦች፤ አገራችንም ኢትዮጵያ ናት::

በሕዝብ ብዛትም ከአፍሪካ ሁለተኛ ስንሆን፣ በቆዳ ስፋት ከሃምሳ አራት አገሮች አስረኛ ደረጃ ላይ ነን:: በዲፕሎማሲያዊ ስልጣኔያችን ለመላው ዓለም በተጨባጭ ካሳየን፣ ከመቶ ዓመታት በላይ የውጭ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት እንዳለን ታሪካችን ያረጋገጥን ብቸኛ አፍሪቃዊት አገር ነን።

አብዛኞዎቹ የአፍሪቃ አገሮች ቢሆኑም በዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ረጅም ዕድሜ ከስድሣ ዓመት በላይ አያልፍም። ኢትዮጵያ ግን ከኢጣሊያና ከፈረንሣይ ከአሜሪካ (USA) እና ከእንግሊዝ ከሩሲያና ከጀርመንን ከመሳሰሉ (ከስድስት አገራት) ጋር ከመቶ ዓመታት ለሚበልጥ ጊዜ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት እንደነበራት ታሪክ ምስክር ነው::

ዛሬ ላይ ግን ክብሯን በማይመጥን ደረጃ የፀረ ሽብር የክፉ ቀን አጋሯ አሜሪካ ውለታዋን እረስታ አውሮፓንና ሸሪኮቿን አስተባብራ በውስጥ ጉዳያችንና በሉአላዊነታን ላይ ዘመቻ ትከፍትብናለች ብሎ ማንም ያሰበም ሆነ የጠረጠረ አልነበረም:: ግን እውነት ስለ መሆኑ በታሪክ ፊት ቆመን እንመሰክራለን::

አሜሪካ በኢትዮጵያ የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ በመግባት ሸንጧን ገትራ አውሮፓን በ«ተባበሩኝ» እየተማፀነች የከፈተችብን የሚዲያ ዘመቻ ሳይበቃ የHR 6600 ረቂቅ ሕግ በምክር ቤቷ ለማፅደቅ እየተንጎራደች በማስፈራራት ላይ ትገኛለች::

በሌላ በኩል ለስልጣንና ለገንዘብ ሲሉ የገዛ ሐገራቸውንና ሕዝባቸውን አሳልፈው በሸጡ ሐገር ከሐዲ ባንዳዎች አማካኝነት አሜሪካ የHR 6600 እረቂቅ ሕግ እንድታፀድቅ ድጋፍ እየሰጡ ይገኛሉ:፡ በተለይም የሕወሓት ጁንታ ቡድንና ሸኔ የአንበሳውን ድርሻ ሲወስዱ ሆድ አደር ምሁራኖችና ፅንፈኛ ብሔርተኞች ታሪክ ይቅር የማይለው የአገር ክሕደት በነጩ ቤተመንግሥት ፊት ለፊት ዋሽንግተን ዲሲ ላይ ቆመው የኢትዮጵያን መንግሥት ሲያወግዙ ማየት እጅግ ያሳፍራል።

እንደ አገር የምናስብ ከሆነ ኢትዮጵያ ይህን ጉዳይ ችላ ብላ በቀላሉ የምታልፈው አይመስለኝም:: ኮስተር ብላ በሳል ምሁራኖቻችን ሰብስባ የHR 6600 ትክክለኛ የአሜሪካንን ክስ እና የውስጥና የውጭ ፖሊሲዋን የተከፋይ ሎቢስቶችን ሴራ ጭምር ብትንትን አድርጋ አስጠንታ ዘላቂ መፍትሔ በማግኘት ለዓለሙ ኅብረተሰብ ማጋለጥ ይኖርባታል::

እስከዚያው እንደ ዜጋ የሚመስለንን ሐሳብ ለሕዝባችን ማንሸራሸርና ግንዛቤ ማስጨበጥ የእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ኃላፊነትና ግዴታም ጭምር በመሆኑ ያለንን ገንቢ ሀሳብ በነፃው አምድ ላይ እናዋጣ:: በዚህም «ለመሆኑ አሜሪካናም ሆነች ሸሪኮቿ የሰብዓዊ መብት ጉዳይና የእኛ የእርስ በእርስ አለመስማማት ልባቸው ውልቅ እስከሚል አሳስቧቸው ነው?» የሚለውን ጥያቄ አብረን እንመልሰው።

እንደእኔ ግንዛቤ ከሆነ ግን መልሱ አይደለም ነው። ላለፉት ረጅም ዘመን በታሪክ እንዳየነው ብዙዎቹ ጦርነቶች የተካሔዱት የነዳጅ ዘይት ባስነሳው ውዝግብ ሳቢያ ነበር:: የእነዚህ ጦርነቶች ምክንያትም፣ ታሪክ ሆኖ ቢያልፍም፤ አሁን ዓለም ያለችበትን ሁኔታ አዳዲስ ጥናቶች እንደሚያስረዱን በሚቀጥለው መቶ አመታት አብዛኛዎቹ ጦርነቶች የሚካሄዱት የውሀ ፖለቲካ በሚያስነሳው ውዝግብ ሊሆን እንደሚችል የመስኩ ባለሞያዎች ሰሚ አጡ እንጂ መወትወት ከጀመሩ ውለው አድረዋል::

ውሀ እንደ ሰብዓዊ መብት የመኖርና ያለመኖር ሕልውና ሊሆን እንደሚችል በእርግጠኝነት ቢናገሩም፤ ከሳሃራ በታች ያሉት አገሮች የአንድ ሰው አማካይ የነብስ ወከፍ የውሀ አጠቃቀም ከ10 እስከ 20 ሌትር ብቻ ሲሆን፣ በአውሮፓ የሚኖር አንድ ሰው 200 ሌትር ውሀ በነፍስ ወከፍ እንደሚጠቀምም በጥናት አረጋግጠዋል:: በዚህ የተነሳ የወደፊቱ ዓለም በተፈጥሮ ሀብታችን ላይ አንድ ነገር እያሰላሰለ መሆኑን ብዙ ምልክቶች እያየን ነው።

ኢትዮጵያ አባይን ጨምሮ ሰባት ታላላቅ ወንዝ ያላት የውሀ ሀብታም አገር አንዷ ስትሆን፤ 85 በመቶ የሚሆን በግብርና የሚተዳደር ሕዝቧ በወንዞቹ አማካኝነት የእርሻ መሬቶቿን አልምታ እራሱን ለመመገብ እንዳትችል ግን በምስቅልቅል የክልል ፖለቲካና የትርክት ታሪክ እየታመሰን ገበሬው በመስኖ የበቀለ እሸት ቆርጦ እንዳይበላ በምግብ እራሱን እንዳይችል በዘር ፖለቲካ ሰንሰለት አስረን በኑሮ ውድነት ስንቀጣው ኃያላን አገሮች ደግሞ በምግብ እራሳችንን እንዳንችል በወንዞቻችን እንዳንጠቀም በሰብዓዊ መብት ሰበብ አስገዳጅ ማዕቀቦችን እያረቀቁ ያስፈራሩናል::

ይሄን እንደ ዜጋ ስናስበው ያሳዝናል። በእርግጥ በእኛም በኩል ያሉብንን ስህተቶች መንግሥት በቶሎ ማረም ባለመቻሉ ሕዝባችን በኑሮ ውድነት እየደረሰበት ካለበት መከራ በተጨማሪ የመንግሥትን ባለስልጣን ሙሰኛና ሌቦችን መቋቋም እንዳቃተው ብሶቱን አደባባይ ላይ አውጥቶ ዘርግፎታል። መንግሥትም ድርጊቱ በሾሟቸው ባለስልጣኖች እንደሚፈፀም አምኖ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለሕዝብ ተወካዮች ፊት ለፊት በፓርላማቸው ላይ ፍረዱኝ ሲሉ ተደምጠዋል::

ነገር ግን እስካሁን የሚወሰዱት እርምጃዎች ከቁጣ ባለፈ ፀረ ሙስና ኮሚሽኑ በአንድም ባለስልጣን በራፍ ድርሽ አላለም:: የክልሎችን ሳናነሳ የአዲስ አበባ ከተማን ብቻ ለናሙና ብንወስድ እንኳን በአፍሪካ ከሚገኙና ከፍተኛ የኑሮ ውድነት ካለባቸው 15 ከተሞች መካከል በቀዳሚነት መቀመጧን ቢዝነስ ኢንሳይደር አፍሪካ የተባለ ድረገጽ በወጣው መረጃ ነግሮናል። በዚህም ድረገጹ ባወጣው አሀዛዊ የኑሮ ውድነት መለኪያ መሠረት አዲስ አበባ በ58 ነጥብ 92 በአንደኛ ደረጃ ተቀምጣለች። ሕዝቡም ይሄን ይናገራል። ለዚህም እንደ ሕዝብ የገጠመንን ውጫውም ሆነ ውስጣዊ ፈተና ለመሻገር፤ እንደ መንግሥት ሕዝብ ላይ የተጫነውን የኑሮ ውድነትና የዋጋ ንረት ለማንሳት ተናብበው መንቀሳቀስ ተገቢ መሆኑን ያምናል።

# ጮክ ብለው የተስተጋቡ ሰሞነኛ እሮሮዎች...!?



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ከብልጽግና 1ኛ ጉባኤ በኋላ በተዘጋጁ ሕዝባዊ መድረኮች ያለልዩነት ዳር እስከ ዳር ጮክ ብለው የተደመጡ እሮሮዎች ከሞላ ጎደል ተመሳሳይ ናቸው ። የደህንነትና የጸጥታ ጉዳይ ፤ ከእለት ወደ እለት እየተባባሰ የመጣው የኑሮ ውድነት ፤ በመንግስት መዋቅር የተንሰራፋው ብልሹ አሰራርና የገነገነ ሙስና ፤ የመልካም አስተዳደር፣ የአገልግሎት አሰጣጥ ፣ የፍትሐዊነትና የእኩልነት ጥያቄዎች ይገኙበታል ። እነዚህ ማስጠንቀቂያዎች ፣ እሮሮዎችና ብሶቶች የተፈጠሩት በጊዜ መፍትሔ ስላላገኙ ነው ። አዎ ! ገና በጥያቄ ፣ በጥቆማና አስተያየት ደረጃ እያሉ በጊዜ ቢፈቱ ኑሮ ዛሬ ላይ ወደ ዋይታና ሙሾነት ባልተቀየሩ። ለዚህ ነው የአገራዊ ምክክር ዋና ኮሚሽነር ፕሮፌሰር መስፍን አርዓያ ሰሞኑን በተሰናዳ የትውውቅ መድረክ ላይ ፤... የሕዝብ ለቅሶና ዋይታ መርገብ ብቻ ሳይሆን መቆም አለበት ።...ያሉት ። በአንዳንድ መድረኮች ከእሮሮነትም አልፈው ማስጠንቀቂያና ማስፈራሪያ ያዘሉ ነበሩ ። በነገራችን ላይ ቀያይ ያበሩም ናቸው ። ይህ ችግሮች ለአመታት ተባብሰው ተባብሰው አደገኛ ደረጃ ላይ መድረሳቸውን ገሀድ ያወጣል ። ለመፍትሔ የሚደረጉ ጥረቶች ይሄን የሚመጥኑ ካልሆኑ ደግሞ ከዚህ በላይ ተባብሰው መጀመሪያ የደህንነትና የጸጥታ ችግር በማስከተል የህልውና ስጋት እንደሚሆኑ አያጠያይቅም ።

እነዚህ እሮሮዎቹ የአንድ ሰሞን ብሶትና ምሬት የወለዳቸው አይደሉም ። ቢያንስ ከአጼው ፣ ከደርግና ከኢህአዴግ ሲንከባለሉ የመጡ ናቸው ። ሆኖም ባለዕዳዎች ይህ ትውልድ ፣ ይቺ ሀገርና ገዢው ፓርቲ ብልጽግና ናቸው ። ዕዳው እንደ የእሳት አሎሎ አንዱ ለአንዱ ሲወረውር ሲወረውር እዚህ ላይ ደርሷል ። ከዚህ በኋላ ግን በእኛ ማለፍ አለበት ። ለነገው ትውልድ፣ ለነገዋ ኢትዮጵያና ለነገው ፓርቲ ልንወረውረው አይገባም ። በእኛ ማለፍና ቀን መውጣት አለበት ። ይህ ግን ስለተመኘን ብቻ አይሆንም ። ከዘመቻ ፣ እሳት ከማጥፋትና ከሆይ ሆይ አሰራር ወጥተን ፤ በተሳካ የቀዶ ጥገና ትክክለኝነት(precision) ልክ በጽኑ ሕሙማን ክፍሎች የሚገኙ ሕመሞቻችንን ማከም አለብን ።

ስለሆነም የፊዚክስ ሊቁ አልበርት አነስታይን " ችግሩን በፈጠረው አስተሳሰብ ፤ ችግሩን መፍታት አይቻልም ። " እንዳለው ፤ በታላቁ መፅሐፍ የማቲዎስ ወንጌል 9 ÷ 17 ላይም እንዲህ እንደተባለው ፤ " በአረጀ አቁማዳ አዲስ የወይን ጠጅ የሚያኖር የለም ። ቢደረግ ግን፣ አቁማዳው ይፈነዳል፣ የወይን ጠጁም ይፈሳል አቁማዳውም ይጠፋል ። ነገር ግን አዲሱን የወይን ጠጅ በአዲስ አቁማዳ ያኖረዋል፣ ሁለቱም ይጠባበቃሉ ።"። በሀገራችን የተካሄደው ለውጥ እንጂ አብዮት ስላልሆነ ፤ ዛሬ ተባብሰው እሮሮና ብሶት የሆኑ የሕዝብ ጥያቄዎችን በጊዜ ያልመለሰው መዋቅርም ሆነ ተቋም ከሞላ ጎዳል ዛሬም በቦታው እንዳለ ነው ።

ስለሆነም ለሕዝብ እሮሮዎች የዳረጉ መዋቅሮችንና ተቋማትን ተሸክሞ የማያዳግም መፍትሔ መስጠት አይቻልምና በጥንቃቄ እንደገና ሊፈተሹና ዳግም ሊወለዱ ይገባል ። ማሻሻያዎች በሙላት እየተፈጸሙና እየተመሩ መሆኑን እርግጠኛ መሆን ያሻል ። ለውጡን ተከትሎ የተደረጉ ዙሪያ መለስ ማሻሻያዎች በሀገሪቱ ላይ ተደቅነው የነበሩ የህልውና አደጋዎች እንዲያባሩ ቢያደርጉም ዘላቂና ወጥ መፍትሔ ግን ማምጣት አልቻሉም ። ከችግሮቻችን ስፋትና ጥልቀት አንጻር በአንድ ጀምበር የሚፈቱ ባይሆንም በሚፈለገው ፍጥነትና ጥራት ግን እየሄዱ አይደለም ።

ኢኮኖሚያዊ ማሻሻያ ቢደረግም የዋጋ ግሽበቱን፣ የኑሮ ውድነቱንና ስራ አጥነቱን ከግስጋሴ ሲገታ አልተመለከትንም ። መከላከያን ጨምሮ በአጠቃላይ የጸጥታ መዋቅሩ ማሻሻያ ያደረግን ቢሆንም የዜጎች በሰላም ወጥቶ የመግባትም ሆነ የደህንነትና የጸጥታ ችግሮች ገና ሙሉ በሙሉ አልተቀረፉም ። በሀገሪቱ የተደቀነው የህልውና አደጋም ተቀለበሰ እንጂ ሙሉ በሙሉ አልተወገደም ። ዴሞክራሲን ፣ ፍትሕን ፣ እኩልነትን ፣ መልካም አስተዳደርን የሚያሰፍኑ የአሰራርና የአደረጃጀት ማሻሻያዎች ቢደረጉም ዛሬም ሕዝብን ያማረሩ ችግሮች እንዳሉ ናቸው ። ሰከን ብሎ ወደራስ ማየት የሚጠይቅ ፈታኝ ጊዜ ላይ ነን ። ውሳኔዎቻችንና እርምጃዎቻችን ይሄን የሚመጥኑ መሆን አለባቸው ። ጣት መቀሳሰሩን ፣ መወነጃጀሉን ፣ ችግር መገፋፋቱን ትቶ በቅንነትና በቁርጠኝነት በአንድነትና በቅንጅት መስራትን ግድ ይላል ።

ሌላው በመድረኮቹ ጮክ ብለው የተደመጡ እሮሮዎች የአንድ ብሔር ወይም ሀይማኖት አልያም ፖለቲካ ፓርቲ እሮሮ ሳይሆኑ የሁሉም ኢትዮጵያዊ ስለሆኑ በአንድነት ምላሽ ሊሰጣቸው ይገባል ። ገዢው ፓርቲም ሆነ ስልጣን ላይ ያለው መንግስት በበለጠ ፖለቲካዊ ቁርጠኝነት መዋቅሩንና ተቋማቱን ሊፈትሽ ይገባል ። ገዢው ፓርቲ ከስህተት አዙሪት ወጥቶ በምሳሌ በመምራት ሕዝብን ከጎኑ ማሰለፍ ይጠበቅበታል ። በሕዝባዊ መድረኮች ካስተዋልነውና ልብ ካልነው የብልጽግና አመራሮች ከብሔር አጥር ለመውጣት ተንጠልጥለው ተመልክተናል ። በሒደት ሙሉ በሙሉ ይወጣሉ ብለን ተስፋ እናደርጋለን ። የማንነትና የብሔር ፖለቲካ ጥደው እያንተከተኩ አይደለም ብልጽግና አንካሳውን ልማታዊ መንግስት እውን ማድረግ እንደማይቻል ባለፉት 27 አረጋግጠናል ።

የሶማሌ ክልላዊ መንግስት ፕሬዚዳንት አቶ ሙስጠፌ መሀመድ እንዲሁም የገንዘብ ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር ኢዮብ ተካልኝ ፤ የአፋር ክልል ምክትል ፕሬዚዳንት ኤሌማ አቡበከር በሱማሌ ክልል ጅግጅጋ ፤ የቢኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ አሻድሊ ሀሰን እና የመከላከያ ሚኒስትር ዶክተር አብርሃም በላይ በአሶሳ፤ የኦሮሚያ ክልል ብልጽግና ፓርቲ ኃላፊ ፍቃዱ ተሰማና የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳድር ዶ/ር ይልቃል በባህርዳር ፤ የብልጽግና ፓርቲ ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ አደም ፋራህና የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ አዳነች አቤቤ በአዲስ አበባ ፤ ወዘተረፈ አወያይነት የተካሄዱ ውይይቶች የአማራው ችግር የኦሮሞውም የስልጢውም፤ የአፋር ችግር የሱማሌውም ፤ የሱማሌው ችግር የአፋሩም ፤ የቤኒሻንጉል ችግር የትግራዋዩም ፤ የኦሮሞው ችግር የአማራውም ፤ የሀረሪው ችግር የአማራውም ፤ የጋምቤላው ችግር የደቡብ ምዕራቡም ፤ የሲዳማው ችግር የደቡቡም ፤ መሆናቸውን ያስገነዘቡ ነበሩ ። የአንዱ ኢትዮጵያዊ ፈተና የሁሉም መሆናቸውን የሚያሳዩ ተምሳሌታዊ መድረኮች ነበሩ ማለት ይቻላል ። ለታይታና ለይምሰል የተተወኑ ድራማዎች እንዳልሆኑ ስለምናም ተጠናክረው እንዲቀጥሉ እናበረታታለን ።

ሁለት አስር አመታትን ያስቆጠረው የዋጋ ግሽበትና የኑሮ ውድነት የዜጋውን ኑሮ በብርቱ እየፈተነው ፤ ከኢኮኖሚያዊ ችግርነት ወደ ለየለት ማህበራዊና ፖለቲካዊ ቀውስነት እንዳይባባስ እያሰጋ ይገኛል ። በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ ኢኮኖሚው ለቀደሙት 27 አመታት የአንድ ቡድንና የጭፍራው መጠቀሚያ በመሆኑ በተከሰተው ኢፍትሐዊ ተጠቃሚነት ላይ አሻጥር፣ ጦርነትና አለመረጋጋት እንዲሁም የራሽያ ዩክሬን ጦርነት በአናቱ ተከልሶበት ኑሮው አልቀመስ ብሏል ። የውጭ ምንዛሬ እጥረት ፤ የተራዘመ የግብይት ሰንሰለት ፤ ከገበሬ ማሳና ከጉልት እስከ ጅምላ አከፋፋይ የተሰገሰገ ደላላ ፤ በግብይት ሰንሰለቱ የተንሰራፋው ስርዓት አልበኝነት ፤ ዋጋን በአድማ መወሰን ፤ ምርትን በመደበቅ ሰው ሰራሽ እጥረት መፍጠር ፤ የፍላጎትና የአቅርቦት አለመጣጣም፤ የኑሮ ውድነቱን ለመከላከል በመንግስት ዘንድ ወጥ የሆነ ፖለቲካዊ ቁርጠኝነት አለመኖር ፤ የሎጅስቲክስ አገልግሎቱ ቀልጣፋ አለመሆን ፤ ወደብ አልባ በመሆናችን በየአመቱ ለወደብ ኪራይ ቢሊዮኖችን የምናወጣ እና ስለሙብቱ የሚቆረቆርና የሚጠይቅ ሽማች አለመፈጠሩ እንደ ዚምባብዌና ቬኒዞላ ባይሆንም በሰዓታት ልዩነት ለሚተኮስ የዋጋ ግሽበት እንዲዳረግ መግፍኤ ሆኗል።

**የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ (State of Emeregency) የሚያስፈልገበት ደረጃ ላይ ይገኛል ፤ ይህም የኢኮኖሚ መረጋጋት ከሌለ ፖለቲካዊ መረጋጋት ስለማይመጣ ነው ። ፖለቲካዊ ፍላጎቶችን አጥቶ መታገስና ኢኮኖሚያዊ ፍላጎቶችን አጥቶ መታገስ እኩል አይደለም። በመሆኑም መንግሥት በዚህ ወቅት ከኢኮኖሚው የቀደመ አጀንዳ ሲኖረው አይችልም**

በየፍጆታ ሸቀጦች ላይ የሚታየው የዋጋ ግሽበት በሌሎች ምርቶችና አገልግሎቶች ላይ ግሽበትንና የኑሮ ውድነቱን እያባባሰው ይገኛል ። በዚህ ሳቢያ በመዋቅራዊና በተቋማዊ ችግር የተነሳ ጽኑ ታማሚ ሆኖ ለኖረው ኢኮኖሚ ሌላ ራስ ምታት ሆኖበታል። የለውጡ መንግስት ባለፉት ሶስት አመታት የኑሮ ውድነቱንና የዋጋ ግሽበቱን ወደ ነጠላ አኃዝ ለማውረድ ያደረገው ጥረት ውጤት አለማስገኘቱን አምኖ የአዲሱ መንግስት ቀዳሚ ተግባርም ይሄን ማስተካከል እንደሆነ ቃል ቢገባም በሚፈለገው ፍጥነትና ቅንጅት እየሄደ አይደለም ። እንደ አማርኛው ሪፖርተር ሀተታ ከሆነ፤ በየወሩ የሚስተዋልበት የዋጋ ግሽበት እየተንከባለለ መጥቶ በወርኃ የካቲት በተለይም በምግብ ነክ ኢንዴክስ ከፍተኛ ጭማሪ ታይቷል ። በአገሪቱ የተመረጡ 119 የገበያ ቦታዎችን መሠረት አድርጎ በቀረበው የየካቲት ወር 2014 ዓ.ም የምግብ ዋጋ ግሽበት ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወር ጋር ሲነፃፀር በ41ነጥብ9 በመቶ ጭማሪ አሳይቷል ። በተለይም በእህሎች ዋጋ ላይ በአብዛኛው ጭማሪ እንደታየ የማዕከላዊ ስታስቲክስ አገልግሎት ሪፖርት ያመለክታል።

የዋጋ ንረቱን ለመቋቋም የሚያስችል ወርኃዊም ሆነ ዕለታዊ የገቢ ጭማሪ ላላገኘው ብዙኃኑ የኅብረተሰብ ክፍል በየወሩ እየተጋፈጠው ያለው የዋጋ ንረትና የኑሮ ውድነት መንግሥት ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ለምላሹ ካልተጋበት ፣ በቀጣይ የሚመጣው ቀውስ ከፍተኛ እንደሆነ ሪፖርተር ያነጋገራቸው የኢኮኖሚና የፖሊሲ አማካሪ ባለሙያዎች አስረድተዋል ። የኢኮኖሚ ጉዳዮች ባለሙያው አቶ ዋሲሁን በላይ ፣ ምንም እንኳን በሚመለከተው የመንግሥት ተቋም በየወሩ ይፋ የሚደረገው የዋጋ ግሽበት አኃዝ ሁሉንም የሚያስማማ ባይሆንም ፣ የተለያዩ አገራዊና ዓለም አቀፋዊ ጫናዎችን እያስተናገደ ያለው የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ እስካሁንም የዋጋ ንረቱ በ30 እና 40 በመቶ መቆየቱ የሚያስገርም ነው ሲሉ ለሪፖርተር ተናግረዋል።

ከሁሉም በፊት መታየት ከሚገባቸው ነገሮች ውስጥ የዋጋ ንረት እንዴት ነው እየተሰላ የሚገኘው የሚለው መሠረታዊ ነገር ነው ያሉት አቶ ዋሲሁን ፣ 300 እና ከዚያ በላይ ሸቀጦች አንድ ላይ ተወስደው ጤፍም ሆነ ድንብላል፣ ስንዴ ሆነ ዱባ በአንድ ምድብ ተጨፍልቀው ሲሰሉ የሚገኘው ቁጥር መሬት ላይ ካለው እውነተኛ የዋጋ ንረት ጋር የማይስተካከል ዝቅተኛ ቁጥር ሊያስገኝ ይችላል ብለዋል። ነገር ግን ስንዴ ፣ ጤፍ ፣ ገብስ ፣ ዘይት፣ ስኳርና መሰል አስፈላጊ አሥር የሚደርሱ ግብዓቶች ተሰልተው የዋጋ ንረቱ ቢሠራ በአማካይ የሚገኘው ቁጥር 100 ፐርሰንት ሊገባ ይችላል ሲሉ አስረድተዋል። በሌሎች አገሮች የዋጋ ንረትን ከቦታ ቦታ ለየብቻው እንደሚቀርብ የገለጹት የኢኮኖሚ ባለሙያው ፣ አዲስ አበባና ምንጃር ላይ አንድ ነዋሪ ለቤት ኪራይ እኩል ወጪ እንደማያወጣ ቢታወቅም ወርኃዊ የስታትስቲክስ ሪፖርት ሲቀርብ ግን መረጃው በመላው ኢትዮጵያ ተብሎ ሲቀርብ ይስተዋላል ብለዋል ።

በአጠቃላይ የዋጋ ንረትን በተመለከተ በእያንዳንዱ ክልል በየራሱ ተሠርቶለት የአገሪቱንም አማካይ ማስቀመጥ ፣ በቦታዎቹ ሊስተካከል የሚገባውን ጉዳይ ለማስተካከል ያስችላል ያሉት የኢኮኖሚ ተንታኙ ፣ ቁጥሮች ላይ ያለው ውዝግብ መታረቅ አለበት ብለዋል። በመሆኑም የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ (State of Emeregency) የሚያስፈልገበት ደረጃ ላይ ይገኛል ፤ የሚሉት አቶ ዋሲሁን ፣ ይህም የኢኮኖሚ መረጋጋት ከሌለ ፖለቲካዊ መረጋጋት ስለማይመጣ ነው ሲሉ ያክላሉ ። ፖለቲካዊ ፍላጎቶችን አጥቶ መታገስና ኢኮኖሚያዊ ፍላጎቶችን አጥቶ መታገስ እኩል አይደለም። በመሆኑም መንግሥት በዚህ ወቅት ከኢኮኖሚው የቀደመ አጀንዳ ሊኖረው አይችልም ብለዋል ።

የኢኮኖሚ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አሁኑኑ !

## የምድር በረከት

# ለማዕድን ልማት የተሰጠ ትኩረት

**ስምስም መንግሥቱ**

የተለያየ ቀለሞች ያሏቸው፣ ፈርጦቻቸው እንደፀሐይ የሚያንፀባርቁ፣ በተለያየ ቅርጽ (ዲዛይን) የተሠሩ፣ እይታን የሚስቡ፣ ለጣት ቀለበት፣ ለአንገት ሀብልና ለእጅ አምባር ተዘጋጅተው ለገበያ የሚቀርቡ ከከበሩ ማዕድናት የተሠሩ ጌጣጌጦች በብዙ ሂደቶች ውስጥ አልፈው ለአገልግሎት እንደሚበቁ ስንቶቻችን እንገነዘብ ይሆን? በቁፋሮ ማዕድኑን ከመሬት ውስጥ ከሚያወጣው ጀምሮ ልፋቱ ብዙ ነው። በቁፋሮ ሥራ ላይ የተሰማሩ በመሬት መደርመስ እስከ ሞት የሚደርስ አደጋ ያጋጥማቸዋል። እንዲህ ያሉ ዜናዎችን መስማት ተለምዷል። ሥራው ብዙ የሰው ኃይል የሚጠይቅ በመሆኑ ጉዳቱም በብዙዎች ላይ ነው የሚደርሰው። እንዲህ ያለው አጋጣሚም የጉዳት መጠኑን የከፋ ያደርገዋል። ማዕድኑ ከሚወጣበት ሥፍራ ተቀብሎ በተለያየ የመስሪያ ማሽን ታግዞ ለተለያየ አገልግሎት የሚያውለው ባለሙያም ቢሆን እንዲሁ ተጨንቆና ተጠብቦ ነው አሳምሮና አስውቦ ለአገልግሎት የሚያበቃው። ለመሆኑ ወደ ጌጣጌጥ መሸጫዎች ጎራ ስንል በከበሩ ማዕድናት እና በወርቅ ማዕድን ከተሠሩ ጌጣጌጦች ዓይናችን የሚያርፈው በየትኛው ላይ ነው? ወደ ወርቅ ጌጣጌጥ የሚያደላው ሰው የበለጠ እንደሚሆን ነው ግምታችን። ለዚህ ደግሞ ምክንያቱ በወርቅ ማጌጥ የተለመደ በመሆኑ ነው። ከከበሩ ማዕድናት የሚሠራ ጌጣጌጥ የሀብት ምልክትና ዋስትና አድርጎ አለመውሰድ፣ በወርቅና በከበሩ ማዕድናት መካከል ያለውን ልዩነት አለመገንዘብ፣ ስለከበሩ ማዕድናት ጥቅምና ያላቸውን ዋጋ አለማወቅ ከምክንያቶቹ ጥቂቶቹ ናቸው። እንደዋዛ የማይታዩ ውስን በሆኑ ሰዎች አቅም የሚገዙና ስለጥቅሞቻቸውም የሚያወቁ ከከበሩ ማዕድናት የተሠሩ ውድ ጌጣጌጦች መኖራቸውን የሚያውቁ ሰዎች መኖራቸውም አይዘነጋም። በግራም መቶ ሺህ ብርና ከዚያ በላይ ዋጋ የሚያወጣ የማዕድን ጌጣጌጥ የመኖሩን ያህል ሰዎች በአቅማቸው ገዝተው ሊጠቀሙበት የሚችል መኖሩንም በዘርፉ ላይ የሚገኙ ሙያተኞች ይገልጻሉ። አንዳንድ የዘርፉ ባለሙያዎች ሲሉ እንደሚሰማው በኢትዮጵያ በከበሩ ማዕድናት ማጌጥ የተለመደ አይደለም። ብዙዎች አይሳቡም። በሌላው ዓለም ላይ ግን ከከበሩ ማዕድናት ለተሠሩ ጌጣጌጦች ያለው አመለካከትና ፍላጎት የተሻለ ነው። በአድናቆትና በፍላጎት ገዝተው ይጠቀማሉ። ኢትዮጵያውያኑ ከሌላው ዓለም ለመለየታቸው ከላይ የተጠቀሱት ምክንያቶች ሊሆኑ እንደሚችሉ ይገመታል። ግን ደግሞ ማዕድን በማውጣት ዘርፍ ላይ የተሰማራውም ሆነ ማዕድኑን ተቀብሎ እሴት የተጨመረበትንና ያልተጨመረበትን ለውጭ ገበያ የሚያቀርበው ለውጭ ገበያ በማቅረቡ ላይ ትኩረት ማድረጉም በአገር ውስጥ ያለውን ሸማች የዘነጋው እንደሆነ ሌላው በምክንያትነት ይነሳል።

ከአገር፣ አህጉርና እስከ ዓለም ተፈላጊ የሆነና ከፍተኛ ዋጋ የሚያወጣ የከበረ ድንጋይ በሚያስገኘው ጥቅም የግለሰብን ኑሮ ከመለወጥ አልፎ ለአገር የምጣኔ ሀብት ዕድገት ከፍ ያለ አስተዋጽኦ አለው። በአንድ ጀንበር ሚሊየነር የሆነውን አንድ ታንዛኒያዊ ማስታወስ ይቻላል። ታንዛኒያዊውን ሚሊየነር ያደረገው «ታንዛናይት» የተባለ የማዕድን ዓይነት ሲሆን፣ በባህላዊ ቁፋሮ ያወጣቸው እያንዳንዳቸው 15 ኪሎ ግራም የሚመዝኑ ሁለት ማዕድናት ናቸው። ታንዛናዊው ሦስት ነጥብ አራት ሚሊዮን ዶላር ሸጦ መጠቀሙንና በወቅቱም መነጋገሪያ እንደነበር ነው ቢቢሲ በድረገጽ ላይ ካሰራጨው መረጃ መረዳት የቻልነው።

ወደአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ስንመጣ እንዲህ እንደ ታንዛኒያዊው ያለ ጎልቶ የሚወጣ ወይንም የሚነገር ተሞክሮ ማቅረብ ባንችልም በባህላዊ የማልማት ዘዴ በዶማና አካፋ መሣሪያ ቆፍሮ ማዕድን በማውጣት ላይ ተሰማርተው የኑሮ መተዳደሪያቸው ያደረጉና ዋና የገቢ ምንጫቸው የሆነ የማኅበረሰብ ክፍሎች የበዙ ናቸው። ሀብቱ በሚገኝበት ስፍራ የሚገኙ ወጣቶችን በማህበር አደራጅቶ በዘርፉ ላይ እንዲሰማሩ በማድረግ መንግሥትም የሥራ ዕድል እየፈጠረበት ይገኛል። እንዲህ ያለው የተለመደ ሂደት በኢትዮጵያ ማዕድን የማውጣት ሥራ ባህላዊውን የተከተለ መሆኑ አንዱ ማሳያ ነው። እንደአገር ከዘርፉ የሚመነጨው ኢኮኖሚም በባህላዊ የቁፋሮ ሥራ ላይ የተመሠረተ ነው። ባህላዊ ሥራው አገራዊ ኢኮኖሚውን ከፍ እንዳላደረገው ይታወቃል። የዘርፉ ሥራ ባለመዘመኑና አገሪቱ ውስጥ



**ባህላዊው የማዕድን ማውጣት ሥራን በጥናት እና ምርምር አስደግፎ ወደ ዘመናዊነት ስመቀየር ሰፊ ሥራ እየተሠራ ነው፤**

ያለው እምቅ ሀብትም በጥናት ተለይቶ ባለመታወቁ ሀብቱ ከመኖሩ በስተቀር የትኛው የማዕድን ዓይነትና መጠኑን በእርግጠኝነት መናገር አይቻልም። ኢትዮጵያ ምን ዓይነት ሀብት እንዳላትና በመጠንም ያለው ሀብት ባለመታወቁ ከዘርፉ በሚፈለገው ልክ ጥቅም እንዳልተገኘ እንዲሁ በተደጋጋሚ ሀሳብ ይቀርባል። ሀብቱን የሚከታተል፣ የሚቆጣጠር፣ የሚያስተዳድርና አልምቶ ጥቅም ላይ ለሚያውል አካል ፍቃድ የሚሰጥ ክፍል ተዋቅሮ አገልግሎት የሚሰጥ ቢኖርም በዘርፉ ላይ መረጃ ፈልገን የምናናግራቸው ክፍሎች ወይ ከሌላ ክፍል ጋር ተጣምረው አገልግሎት የሚሰጡ ናቸው። አንዳንዶችም በበቂ ባለሙያና ዕውቀቱ ባላቸው አካላት የሚመሩ ሆነው አናገኛቸውም። በየአካባቢያቸው የሚገኘውን ሀብትም ጠንቅቀው ለማወቅ አቅሙም ያላቸው እንዳልሆኑ ይነገራል። ዘርፉን ለመምራት ከተቋቋሙት ይልቅ የአካባቢው አርሶአደር ሀብቱን በመጠቆም በተሻለ ሚና እየተወጣ እንደሆነ ከአንዳንድ አካባቢዎች የምናገኛቸው መረጃዎች ይጠቁማሉ። አርሶአደሩ የአቅሙን ያህል በባህላዊ መንገድ በመቆፈር የሚያደርገው ጥረት ሥራ ነው የሚያመዝነው። አንዱ ከሌላው በመጠንና በዓይነት ይለያይ ካልሆነ በስተቀር በሁሉም የአገሪቱ አካባቢዎች ለግንባታ፣ ለኢንዱስትሪ ግብአት፣ ለጌጣጌጥና ለተለያየ አገልግሎቶች የሚውሉ የማዕድን ሀብቶች ይገኛሉ። ይሁን እንጂ የምጣኔ ሀብቱን ከፍ ሊያደርጉ የሚችሉ ሀብቶች በአግባቡ ጥቅም ላይ ውለዋል ለማለት የማያስደፍሩ እንደሆነ ፀሐይ የሞቀው ጉዳይ እንደሆነ አይዘነጋም። ሥራው አጥጋቢ ከመሆን ይልቅ ቁጭት የሚያሳድር እንደሆነ ነው መረዳት የሚቻለው።

ለአገር በመቆርቆር ከሚሠራው ሥራ በላይ ሕገወጥነቱ በዝቶ ፈተና ሲሆን ነው የሚሰማው። በቅርብ ጊዜ የወጡ መረጃዎች እንደሚያሳዩት ኦፓል የተባለው ማዕድን አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በሕገወጥ በስፋት እየተሸጠ መሆኑን ነው። በመገናኛ ብዙኃን ሽፋን ያገኘው ይህ ዘገባ ሕገወጥነቱ መስፋፋቱን ነው። በሀብቱ ለመክበር የሚሯሯጡትም አገር ውስጥ ያሉ ዜጎች መሆናቸውም ከመንግሥት የተደበቀ አይደለም። በዚህ ሁኔታ እስከመቼ? አሁን ኢትዮጵያ ካለችበት ተጨባጭ ሁኔታ ማዕድን ከማውጣት ጀምሮ ገበያና ግብይቱን መስመር ማስያዝ ብቻ ሳይሆን፣ ሀብቱን በጥናትና ምርምር ለይቶና አውቆ ተጠቃሚነትን ከፍ ማድረግ ይጠበቃል። መንግሥትም ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥቶ በሰፊው መንቀሳቀስ ጀምሯል። የማዕድን ዘርፉን ለአገር ምጣኔ ሀብታዊ ዕድገት እያደረገ ያለውን አስተዋጽኦ በማዘመን ለመጠቀም ማዕድን ሚኒስቴር ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጋር በጋራ ለመስራት የመግባቢያ ሰነድ በቅርቡ ተፈራርሟል። የስምምነቱ ዋና ዓላማም በባህላዊ መንገድ የሚከናወን ማዕድን የማውጣት ሥራ በዘመናዊ መንገድ አቀላጥፎ ለመስራት እንዲያስችል በዩኒቨርሲቲው በኩል የጥናትና ምርምር ሥራዎች እንዲሠሩ ነው። የጥናት ውጤቱም ለማዕድን ሚኒስቴር የሚሰጥ ነው። የመግባቢያ ሰነዱንም በማዕድን ሚኒስቴር በኩል ሚኒስትሩ ታከለ ዑማ፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በኩል ደግሞ የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ፕሮፌሰር ጣሰው ወልደሃና ናቸው የካቲት 25 ቀን 2014 ዓ.ም የተፈራረሙት።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ ዲን የሆኑት ዶክተር ኃይሉ ኤልያስ በስምምነቱ ዙሪያ ተጨማሪ ማብራሪያ ሰጥተውናል። ዶክተር ኃይሉ እንዳሉት፤ ዩኒቨርሲቲው ከመማር ማስተማሩ ጎን ለጎን ችግር ፈቺ የሆኑ የምርምር ሥራዎችን እያካሄደ እና የማኅበረሰብ አገልግሎት በመስጠት ላይ ነው። በዩኒቨርሲቲውና በማዕድን ሚኒስቴር መካከል የተፈረመው ስምምነትም ይህንኑ አገልግሎቱን የሚያጠናክር ነው። በኢትዮጵያ የማዕድን ቁፋሮ ትኩረት የተሰጠው የውጭ ምንዛሪ በማስገኘት እና በአገራዊ ገቢ ላይ ከፍተኛ ድርሻ ባለው የወርቅ ማዕድን ዘርፍ ላይ ሲሆን የቁፋሮ ሥራው ግን የሚከናወነው በአብዛኛው በባህላዊ መንገድ ነው።

ዘርፉ የሥራ ዕድል በመፍጠር ረገድም ድርሻው የላቀ ቢሆንም በቁፋሮ ሥራው ላይ የሚሰማሩት ሰዎች ግን ባልተጠና የቁፋሮ ሥፍራ እና ያለበቂ የሙያ እገዛ ሥራቸውን እንደሚያከናውኑ ይታወቃል። ከቁፋሮ ጀምሮ ባለው የገበያ ሰንሰለት ውስጥ የሚሳተፈው የኅብረተሰብ ክፍል በርካታ ሲሆን ሕገወጥነቱም የከፋ መሆኑ ደግሞ መንግሥት ማግኘት የሚገባውን ገቢ እያሳጣው ይገኛል። ሳይሠራ ያልለፋበትን ለማግኘት በመካከል ላይ ሆኖ የሚደልለውም ለዘርፉ ሌላው ማነቆ ሲሆን ይህ ደግሞ በዘርፉ ላይ የሚለፋውን የኅብረተሰብ ክፍል ጥቅም እያሳጣ ይገኛል። በአጠቃላይ በዘርፉ ላይ የሚስተዋለው ክፍተት ሰፊ ነው። ከኢኮኖሚ፣ ከሕግ፣ ከተቋማዊ አደረጃጀት፣ እንዲሁም ከአካባቢ ተጽዕኖ፣ ከአካባቢው ማኅበረሰብ ተጠቃሚነት፣ ከሥራ ደህንነትና ከሌሎችም ተያያዥነት ካላቸው ጉዳዮች አኳያ ያሉትን ክፍተቶች ለይቶ ችግሩን ለማሳየትና የመፍትሄ ሀሳብ ለመጠቆም የመጀመሪያ ደረጃ መረጃ የመሰብሰብ የጥናት ሥራ በመካሄድ ላይ ይገኛል። መረጃ የመሰብሰቡ ሥራም ሀብቱ በስፋት በሚገኝባቸው በጋምቤላ፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ ኦሮሚያና ደቡብ ክልሎች ላይ ሲሆን የመረጃ መሰብሰቡን ሥራ በመምራት ላይ የሚገኙትም ከዩኒቨርሲቲው የተውጣጡ ልምድ ያላቸው ባለሙያዎች ናቸው።

መረጃ በመሰብሰብ ሂደቱ ላይ ያጋጠሙ ችግሮች በተለይም ኢትዮጵያ በሰሜኑ ክፍል በተፈጠረው ጦርነት ምክንያት በጦርነት ውስጥ የቆዩ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የፀጥታ ስጋቱ ሙሉ ለሙሉ የተቀረፈ ባለመሆኑ የተፈጠረ ተጽዕኖ ይኖር እንደሆን ዶክተር ኃይሉ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ፤ የፀጥታ ችግሩ ቢኖርም ተቋቁሞ የጥናት ሥራውን ለማከናወን በጥናቱ ላይ ከሚሳተፉት ባለሙያዎች በተጨማሪ የአካባቢውን ማኅበረሰብ በመያዝ መንቀሳቀስ አንዱ አማራጭ ነው። የመንግሥትም እገዛ አልተለየም። በተለይም የማዕድን ሚኒስቴር ከዩኒቨርሲቲው ጋር በቅርበት እየሠራ ይገኛል።

የጥናት ሥራውን ለማጠናቀቅ የተያዘውን የጊዜ ገደብና ቀጣይ ተግባራትን በተመለከተም ዶክተር ኃይሉ እንዳስረዱት፤ እስከ ሰኔ ወር መጨረሻ 2014 ዓ.ም ድረስ መረጃ የመሰብሰቡን ሥራ ለማጠናቀቅ የታቀደ ሲሆን፣ መረጃ የመሰብሰቡ ሂደት እንደተጠናቀቀ የመረጃ ትንተና ሥራ ይሠራል። የመጀመሪያው ሪፖርትም ይቀርባል። የምክክር መድረክም ተዘጋጅቶ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት ይካሄዳል። ለፖሊሲ አውጪዎችና ለሚመለከታቸው አካላትም የሚቀርብ ይሆናል። ከውይይቱ የሚገኘው ግብአትም በጥናት ሥራው ላይ ተካትቶ በአመቱ መጨረሻ የመጀመሪያው ዙር የጥናቱ ሥራ የሚጠናቀቅ ይሆናል።

ችግሮችን መሠረት አድርጎ በሚከናወነው በዚህ የጥናት ሥራ ዋና ትኩረቱ ባህላዊ አሠራርን በማዘመን ከሀብቱ ተጠቃሚ ለመሆን እንደሆነ የሚናገሩት ዶክተር ኃይሉ፤ እንዴት ማዘመን እና ምርታማነቱን ከፍ ማድረግ እንደሚቻል በዝርዝር በመለየት ላይ ትኩረት የሚያደርግ ጥናት እንደሆነ ገልጸዋል። እርሳቸው እንዳሉት የማዕድን ሚኒስቴር በሥራው ላይ ለተሠማሩት የቴክኖሎጂ እገዛም ለማድረግ ያቀደ ሲሆን ከመስከረም 2015 ዓ.ም ጀምሮ የሚካሄደው የሁለተኛው ዙር የጥናት ሥራ ደግሞ የቴክኖሎጂ እገዛው እና የመጀመሪያው ዙር የጥናት ሥራ ያስገኛቸውን ውጤቶች የሚፈትሽ ይሆናል።

የምርምር ሥራዎች ወደ ውጤት እንዲለወጡ የሚደረገው ሙከራ በአብዛኛው ስኬታማ ሲሆኑ አይስተዋልም። በተጨማሪም በምክረሀሳብ ደረጃ የሚቀርቡ ቴክኖሎጂን የመጠቀም ዘዴም በተለያየ ምክንያት ተግባራዊ ሳይሆን የሚቀርባቸው አጋጣሚዎች ብዙ ናቸው። ከዚህ አንጻር ለማዕድን ሥራው የሚያስፈልጉ በቴክኖሎጂ እንዲታገዙ በተለይም የሥራ ማሽኖችን ከውጭ ለማስመጣትም ከግዥና ከውጭ ምንዛሪ ጋር የሚያያዝ ጉዳይ ስለሚቀርብ የአገር ውስጥ የፈጠራ ሥራዎችን በማቅረብ ክፍተቱን ለመሙላት የሚደረግ ጥረት በተለይም በዩኒቨርሲቲው በኩል ይኖር እንደሆን ዶክተር ኃይሉ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ፤ ዩኒቨርሲቲው አሁን ባለው ስምምነት የጥናት ሥራው ላይ የሚያተኩር ሲሆን የቴክኖሎጂ እገዛውን የማዕድን ሚኒስቴር የሚያቀርብ ይሆናል። ለወደፊት ግን በዩኒቨርሲቲው ውስጥ የዩኒቨርሲቲ ኢንዱስትሪ ትስስር ሥራ የተጀመረ ሲሆን ከቴክኒክና ሙያ ጋር በማያያዝ የቴክኖሎጂ እገዛ ሥራዎችን ለመሥራት ሀሳቡ አለ።


የትምህርት ተቋማት የምርምር ሥራዎቻቸውን በጥናትና ምርምር ጆርናል ላይ ከማሳተም ባለፈ ከተቋማት ጋር ተቀራርበው መሥራታቸው ስላለው ጠቀሜታም ዶክተር ኃይሉ እንደገለጹት፤ ዩኒቨርሲቲዎች ከተቋማት ጋር ተቀራርበው መሥራታቸው በዘርፉ ውጤት ለማስመዝገብ ከማገዝ በተጨማሪ ለመማር ማስተማር ሥራውም እንደ ግብአት ያገለግላል። መምህራን በምርምር ሥራው ላይ ያገኙትን ልምድ ለተማሪዎቻቸው ያካፍላሉ፤ ተማሪዎችም በዘርፉ ላይ ስላለው ዕድል የተሻለ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ያስችላቸዋል። ፖሊሲ ለማዘጋጀትም ሆነ ለማሻሻልም የተደራጀ መረጃ ያስፈልጋል። ተቋማትም በመረጃ ላይ የተመሠረተ ሥራ ለመሥራት ያግዛቸዋል።

ማህበራዊ

# ወጣቶች



ወርቅን ከኳርትዝ /ኮረት/ የሚለይ ማሽን



በቀን መቶ ቶን የደለል አፈር ማጠብ የሚችል ማሽን

## ወርቅን አንጠርጥሮ እና አጥቦ የሚያወጣ ማሽን የሠሩ ወጣቶች

**ኢያሱ መሰለ**

ቢቂላ ዮሐንስ እና አባስ ሲራጅ የተወለዱት ኦሮሚያ ክልል፣ ወለጋ ዞን ሲሆን የተዋወቁት ሁለቱም በብየዳ ሥራ ላይ ተሰማርተው እያለ ቡራዩ ከተማ ነው። ቢቂላ በትምህርት አባስ በልምድ ያገኙትን የብየዳ እውቀት አቀናጅተው ወርቅን ከኮረት አንጠርጥረውና ከደለል አጥበው የሚያወጡ አራት ማሽኖችን ሠርተው ጥቅም ላይ አውለዋል። በዛሬው ዝግጅታችንም የጓደኛሞቹን የሥራ ትጋት፣ ፈጠራና ስኬት የምናስቃኛችሁ ይሆናል።

ቢቂላ በነቀምቴ ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ፣ ጀነራል ሜካኒክስ ዲፓርትመንት በሌቭል ሦስት የሜታል ትምህርቱን ተከታትሎ በመመረቅ በሜቴክ ብረታብረትና ኮርፖሬሽን በመቀጠር በብየዳ፣ በፕላስማ ኦፐሬተርነትና በፋብሪኬቲንግ ሙያዎች ሠርቷል። ጎን ለጎንም በመከላከያ ኢንጂነሪንግ ኮሌጅ ትምህርቱን እስከ ሌቭል አምስት ተምሯል።

ሜቴክ ለህዳሴው ግድብና ለስኳር ፕሮጀክቶች የሚውሉ ግብአቶችን ለማምረት ሠራተኞች ሙያዊ ሥልጠናዎችን እንዲያገኙ ሲያደርግ ቢቂላም በኤሮፒያን ዌልዲንግ ሶሳይቲ /EWS/ የተለያዩ የብየዳ ዓይነቶችን እንዲማር ይደረጋል፤ በዚሁ መሠረት መገናኛ አካባቢ በሚገኘው ጀርመን ስልጠና ማዕከል ገብቶ የኢንተርናሽናል ብየዳ ስልጠናውን ይወስዳል። ከዚያም በሜቴክ ስር ሆኖ በበለስ አንድ ስኳር ፋብሪካ ፕሮጀክት፣ በኢሉ አባቦራ ዋዮ የማዳበሪያ ፋብሪካ እንዲሠራ ይደረጋል። ከዚያም በኮካ ፋብሪካና በኢትዮጵያ አየር መንገድ ተቀጥሮ የመሥራት ዕድል ያገኛል። ባህርዳር ከተማ በመሄድ በነበረው የብየዳ ሙያ በአንድ ድርጅት ውስጥ ተቀጥሮ ጀልባዎችን ሠርቷል። ቢቂላ በዩሮፒያን ብየዳ ማዕከል የተለያዩ የብየዳ ዓይነቶችን መማሩና ዓለምአቀፍ ሰርተፊኬት መያዙ በዘርፉ ተፈላጊ እንዳደረገው ይናገራል።

እዚህ አገር በአመዛኙ የሚታወቀው በኤሌክትሮድ የሚበየደው ዓይነት እንደሆነ የሚናገረው ቢቂላ ከአንድ መቶ በላይ የብየዳ ዓይነቶች አሉ ይላል። ለምሳሌ አልሙኒየም የሚበየድበት ማሽን እራሱ ሽቦ እየተፋ የሚያጣብቅ ነው። የማይቀልጥ ኤሌክትሮድ እየተጠቀመ ብረትን በሙቀት እያቀለጠ እርስ በርሱ እንዲጣበቅ የሚያደርግም ሌላ ዓይነት የብየዳ ጥበብ እንዳለም ይገልጻል። ቢቂላ በየሮፒያን የብየደ ማዕከል ሲማር እነዚህንና ሌሎች በርካታ የብየዳ ዓይነቶችን ተምሯል። በዚህም ስድስተኛና የመጨረሻውን የበያጅነት ደረጃ አግኝቷል።

ቢቂላ በተለያዩ ድርጅቶች እየተቀጠረ መሥራት ከጀመረ በኋላ በሚያገኘው የወር ደመወዝ ብቻ መኖር እርካታ አልሰጠው ይላል። ያካበተውን ሙያ ጥቅም ላይ ቢያውለው የተሻለ ነገር ማድረግ እንደሚችል አስቦ ፊቱን ወደ ግል ሥራ ያዞራል።

የትምህርት ሰርተፊኬቱን በማሳየት ከሚኖርበት ቡራዩ ከተማ የሜካኒካል ኢንጂነሪንግ ፈቃድ ያወጣል። ከቤተሰብና ከሚያውቃቸው ሰዎች ላይ ገንዘብ ተብድሮ የተወሰኑ ማሽኖችን ከገዛ በኋላ በቤተሰብ ቦታ ላይ የግል ሥራውን "ሀ" ብሎ ይጀምራል። የራሱን ዲዛይን እያወጣ ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውሉ ትንንሽ ማሺኖችንና የመኪና ስፖንዳዎችን የመሥራት ሙከራ ውስጥ ይገባል።

በዚህ አጋጣሚ ከአባስ ጋር ይተዋወቃል። አባስ የልምድ ሙያተኛ ነው። በቡራዩ ከተማ በተወሰነች ቦታ ላይ መስኮትና በሮችን እየበየደ የሚተዳደር ወጣት ነው። ወጣቶቹ ልምድና እውቀታቸውን አቀናጅተው ቢሠሩ ውጤታማ እንደሚሆኑ ይነጋገራሉ። በጋራ ሠርተው ውጤት ለማምጣት አስበው ቢንቀሳቀሱም ሥራው እነርሱ እንዳሰቡት አልሄድ ይላቸዋል። በእነርሱ ተማምኖ የመኪና ስፖንዳ የሚያሠራ ሰው ይቅርና ትንንሽ ሥራዎችን እንኳ እንደልብ እያገኙ መሥራት ሳይችሉ ይቀራሉ። ግን ተስፋ አልቆረጡም። ቢቂላ ዲዛይኖችን እያወጣ የሻማ ማቅለጫያና መሥሪያ ማሽኖችን ለመሥራት ሞከሩ፤ የሚገዟቸውም ይሁኑ ማሺኑ እንዲሠራላቸው የሚያዙ ሰዎች ግን አልነበሩም። ያም ቢሆን በኪሳራ ውስጥ የራሳቸውን ፈጠራ ከመሥራት አልታቀቡም። አንድ ቀን አንድ አዲስ ነገር ሠርተው ተፈላጊ እንደሚሆኑ በማሰብ ሁሌም ተግተው ይሠሩ ነበር።

ዛሬ እንደ ምኞታቸው ጥረታቸው ፍሬ አፍርቶ ተፈላጊ ሆነዋል። ቢቂላ የስኬታቸውን ሂደት እንዲህ ያስረዳል።

‹‹በአንድ ወቅት እዚሁ ቡራዩ ከተማ ጫላ ከሚባል ሰው ጋር ተዋወቅን፤ ጫላ የቤኒሻንጉል አካባቢ ነዋሪ ነው፤ ከጓደኞቹ ጋር ተደራጅቶ በወርቅ ቁፈራ ሥራ ላይ ተሰማርቷል። አፈር ማጠቢያ ማሽን ቢያገኝ ውጤታማ ሥራ እንደሚሠራ አጫወተኝ። የቁሳቁስ መግዣውን አግዘንና ማሽኑን እኛ እንሥራልህ አልኩት። በብየዳ ሙያ ጥሩ እውቀት እንዳለኝ ቢያውቅም ሊያምነኝ አልቻለም። በጣም እየተቀራረብን ስንመጣና አንዳንድ ሥራዎቻችንንም ሲመለከት እያቅማማም ቢሆን እንድንሠራለት ተስማማን።

ወደ ሥራ ከመግባታችን በፊት የወርቅ ማጠቢያ ማሽኖችን ከኢንተርኔት ላይ እያወረድኩ ቪዲዮውን በመመልከት አጠቃላይ የሚሠሩበትን ቁሳቁስና እንዴት እንደሚሠሩ አጠናሁ። ያንን መነሻ በማድረግ አስፈላጊ ቁሳቁስ ካሟላን በኋላ እኔ ዲዛይን እያወጣሁ አባስም በብየዳ እየረዳኝና ተጨማሪ ሀሳቦችን እየሰጠኝ ‹‹ፕሮሚል›› የሚባል አነስተኛ መጠን ያለው ማሽን ሠራን። ማሽኑ ኳርትዝ /የድንጋይ ኮረት/ ውስጥ የሚገኝ ወርቅን በውሃ እያጠበና እያንጠረጠረ ወርቁን በአንድ በኩል የሚለይ ነው። ጫላ ማሽኑ ተሠርቶ ሥራ እስኪጀመር ድረስ እምነት አልነበረውም። ማሽኑን ወርቅ ወደ'ሚቆፈርበት ቦታ ወስደን ሙከራ ስናደርግ እንዳሰብነው ሀሳባችን ተሳካልን። ጫላም ደስተኛ ሆነ። የእርሱን ውጤታማነት የተመለከቱ ሌሎች ወርቅ ቆፋሪዎችም ተመሳሳይ ትእዛዝ ማቅረብ ጀመሩ። ሌላም ተመሳሳይ ማሺን ሠርተን ሸጥን። ሰዎች በሥራችን መተማመን ጀመሩ።

በቀጣይ ደግሞ ከኮረት ወይም ከኳርትዝ ሳይሆን ከደለል ወርቅን እያጠበ የሚያወጣ ማሽን እንድንሠራላቸው ጥያቄ አቀረቡልን። ከወርቅ አምራች ማህበሩ ጋር በጋራ የሚሠራ አንድ ባለ ሀብት አስፈላጊውን ቁሳቁስ ገዛልንና ማሽኑን ሠራን። ስሙንም ‹‹ቢኤስዲ አንድ መቶ አልነው›› ይላል ቢቂላ።

ከቀደመው ሥራቸው በመማር ከጊዜ ወደ ጊዜ ምርታቸውን እያሻሻሉ መሆናቸውን ይናገራል። ቢቂላና አባስ ሙሉ ጊዜያቸው የወርቅ አፈር ማጠቢያ ማሽን በማምረት ማሳለፍ ከጀመሩ ወዲህ በሥራና በሃሳብ እየተረዳዱ የተሻለ አቅምና ፍጥነት ያላቸውን ማሺኖች እያመረቱ ነው። በተለይም ከወርቅ አምራች ማህበር ጋር ተዳብለው የሚሠሩት ባለሀብት ዛሬ ላገኙት እውቅና አስተዋጽኦ ስላበረከቱላቸው ያመሰግኗቸዋል።

ሦስተኛው ማሽን ተሠርቶ ውጤታማ ከሆነ በኋላ ሌሎች ወርቅ አምራች ማህበራት ተመሳሳይ ጥያቄ አቅርበውላቸው አራተኛውን ማሽን ለመሥራት ይበቃሉ። ማሽኑ በሰዓት ከሰባ እስከ መቶ ቶን አፈር ማጠብ ይችላል። ይህም በቀን አምስት መቶ ሰው ማጠብ የሚችለውን አፈር የሚያጥብ ነው። በኤሌክትሪክ ወይም በጀኔሬተር መሥራት ይችላል።

የደለል ወርቅ የሚገኘው አብዛኛውን ጊዜ ወንዝ አካባቢ በመሆኑ ማሽኑ ወንዝ ዳር ተተክሎ በተገጠመለት ፖምፕ ውሃ እየሳበ ያጥባል። ምንም ዓይነት ኬሚካል ስለማይጠቀም ከአካባቢ ጥበቃ አንጻር የሚያሳድረው ተጽእኖ የለም። አራተኛው ማሽን እስከ 200ሺ ዶላር ግምት ያለው ነው።

እነ ቢቂላ እስከ አሁን ድረስ ለሠሯቸው ማሺኖች የባለቤትነት እውቅና (ፓተንነት ራይት) ለማግኘት እንቅስቃሴ አለመጀመራቸውን ይናገራሉ። ለዚህ ዋና ምክንያታቸው የጊዜ እጥረት ነው። የሠሩትን ሥራ በየባዛሩና በየተቋሙ እያስተዋወቁ እውቅና ለማግኘት ከመሯሯጥ ይልቅ ቅድሚያ መስጠት የፈለጉት ለደንበኞቻቸው ፍላጎት መልስ መስጠት ነው። በርከት ያሉ ማሽኖችን በመሥራት ከውጭ የሚገባውን ማሽን መተካትና የብዙዎችን ጥያቄ መመለስ ጊዜ የሚሠጠው ጉዳይ አይደለም ይላሉ።

የምርቶቻቸውን አቅምና ቴክኖሎጂ በማሳደግ የአገር ውስጥ ፍላጎትን አሟልተው ወደ ሌሎች አፍሪካ አገራት የማስራጨት እቅድ እንዳላቸው ተናግረዋል። በተለይም በምሥራቅ አፍሪካ ደረጃ የወርቅ አፈርን ለማጠብ የሚያስችሉ ማሽኖችን የሚያመርት አንድ ካምፓኒ የመፍጠር ህልም አላቸው። ስለሆነም ሁልጊዜ ራሳቸውን ከቴክኖሎጂ ጋር በማስተዋወቅና በመሥራት አቅማቸውን ማሳደግ ይኖርባቸዋል።

በመጀመሪያው ሥራቸው ኪሳራ እንጂ ጥቅም እንዳላገኙ የተናገረው ቢቂላ ከሦስተኛ እና አራተኛ ሥራቸው ግን ጠቀም ያለ ትርፍ አግኝተው ለሥራው የሚስፈልጓቸውን መበየጃ ማሽኖችና የተለያዩ ቁሳቁሶች በመግዛት እራሳቸውን እንዳጠናከሩበት ይገልጻል። የማሽኑ ፈላጊዎች ቁጥር እየበዛ መጥቷል ያለው ቢቂላ ከሰሞኑ ከጋምቤላና ጉጂ አካባቢ የመጡ ወርቅ አምራች ማህበራት ማሽኑን ለማሠራት አነጋግረውናል ብሏል። የሚድሮክ ካምፓኒ ሠራተኞች ነን ያሉ ሰዎችም ደውለውላቸው ስለጉዳዩ ማብራሪያ እንደተሰጣቸውና ከውጭ እያስመጡ የሚጠቀሙትን ማሽን በአገር ውስጥ ምርት ለመተካት ፍላጎት እንዳላቸው ገልጸውልናል ብሏል።

ይሁንና የብረት ዋጋ መጨመርን ተከትሎ ማሽኑን ሠርቶ ለማጠናቀቅ የሚፈጀው ዋጋ ቀደም ሲል ከነበረው በከፍተኛ ደረጃ እየጨመረ መምጣቱ በሥራቸው ላይ እንቅፋት መሆኑን ተናግሯል።

ጓደኛሞቹ የፈጠራ ሰዎች የድንጋይ ከሰል ለማምረት የሚያስችሉ ማሽኖችንም የመሥራት ፍላጎት አላቸው። በአገር ውስጥ እየተመረተ ያለው የድንጋይ ከሰል ስለማይታጠብ ከውጭ ከሚመጣው ምርት ጋር እየተቀላቀለ ለሲሚንቶ ፋብሪካዎችና ለአንዳንድ የሴራሚክ ፋብሪካዎች ኃይል የመስጠት አገልግሎት እንዳለው የተናገረው ቢቂላ በቀጣይ የድንጋይ ከሰል ማጠቢያ ማሽን በመሥራት ከውጭ በከፍተኛ ወጪ የሚገባውን ምርት ለማስቀረት እቅድ እንዳላቸው ገልጿል። አገር ውስጥ የድንጋይ ከሰል ሲመረት ደቃቁን ክፍል አጥቦ የሚያስወግድ ቴክኖሎጂ ባለመኖሩ የድንጋይ ከሰል የሚጠቀሙ ፋብሪካዎች ለጉዳት እየተዳረጉ መሆናቸውን ከባለሙያዎች ተገልጾልናል የሚለው ቢቂላ ደቃቁን ክፍል አጥቦ ማስወገድ የሚያስችል ማሽን ለመሥራት መዘጋጀታቸውንም ይናገራል።

የድንጋይ ከሰል ማሽን ከውጭ ለማስገባት እየተንቀሳቀሱ ያሉ ኢንቨስተሮች መኖራቸውን ጠቅሶ አንድ ባለሀብት ለጊዜው ከውጭ የማስገባት ፍላጎታቸውን ገትተው እነርሱ ለመሥራት ያሰቡትን ማሽን ለመጠቀም መዘጋጀታቸውን ተናግሯል።

ቢቂላ ሥራቸውን እያስፋፉ ሲሄዱ በዚያው ልክ ሰፊ ቦታና ተጨማሪ የሰው ኃይል እንደሚያስፈልጋቸው፤ አሁን ተከራይተው ለሚሠሩበት ሙሉ ግቢ በወር አርባ ሺህ ብር እየከፈሉ መሆናቸውን የሚናገረው ቢቂላ የሚመለከተው አካል የቦታ ድጋፍ በማድረግ በሥራና በሥራ ዕድል ፈጠራው ዘርፍ የሚያደርጉትን ጥረት ቢያግዛቸው የበለጠ ውጤታማ እንደሚሆኑ ይገልፃል።

መቁረጫ፣ ማጠፊያና መጠቅለያ ማሽኖች ስለሌሏቸው ሌላ ቦታ እየሄዱ በክፍያ እንደሚያሠሩ ተናግሯል። ብድር ቢመቻችላቸው እነዚህን ማሽኖች በእጃቸው በማድረግ ለበርካታ ወጣቶች የሥራ ዕድል መፍጠርና የእውቀት ሽግግር ማድረግ እንደሚችሉም ቢቂላ ይናገራል።

ማሽን ሲሠራም ይሁን ተተክሎ አገልግሎት መስጠት ሲጀምር የሰለጠኑ ሙያተኞች ያስፈልጉታል የሚለው ቢቂላ ማሽኑ ላይ ለሚሠሩትም ይሁን ሲበላሽ ለሚጠግኑት ሙያተኞች ስልጠና በመስጠት በሥራው ሰንሰለት ውስጥ ለሚያልፉ በርካታ ሰዎች የሥራ ዕድል መፍጠር ያስችላል ብሏል።

እኛም እንዲህ ዓይነቱ ፈጠራ ቢበረታታ በቴክኖሎጂ እውቀት የበለጸገ ትውልድ ለመገንባት የሚደረገውን ጥረት የሚያግዝና የኢትዮጵያን ሁለንተናዊ እድገት ከማፋጠን አኳያ ጉልህ ድርሻ የሚኖረው መሆኑን በመመስከር አስፈላጊው ድጋፍና ትብብር ቢደረግላቸው ተገቢ ነው እንላለን። ሌሎች ወጣቶችም የቢቂላ ዮሐንስን እና አባስ ሲራጅ አርአያነት ይከተሉ ዘንድም አደራ እንላለን። ሰላም!!!

# ‹‹ዱቡሻ›› የጋሞ አባቶች እርቅና ሰላም የሚያወርዱበት ሥርዓት

**ኢያሱ መሰለ**



በየአካባቢው የሚኖረው ኢትዮጵያዊ ቂምና በቀልን አራግፎ እርቅና ሰላምን የሚያወርድበት የየራሱ ቱባ ባህላዊ እሴት አለው። ኦሮሞው፣ አማራው፣ ሶማሌው፣ አፋሩ፣ ትግሬው፣ ሲዳማው፣ ጋሞው፣ ጋምቤላው ወዘተ እርስ በእርሱና ከሌላው ማህበረሰብ ጋር በሚፈጥራቸው ጊዜያዊ ግጭቶች ባህላዊ የእርቅና የሽምግልና ሥርዓቶችን እያከናወነ አብሮነቱን ሲያስቀጥል ኖሯል። አሁንም እያስቀጠለ ነው። ኢትዮጵያ ስለዴሞክራሲ፣ ስለመልካም አስተዳደር፣ ስለእርቅና ሰላም ከየትኛውም አገር ሳትበደር ጥቅም ላይ ልታውላቸው የሚገቡ ጥሩ ጥሩ ተሞክሮዎችን ማግኘት የምትችልባቸው ባህላዊ እሴቶች አሏት። ከእነዚህ ውስጥ አንዱ የጋሞ አባቶች የሽምግልና ሥርዓት /ዱቡሻ/ ነው።

በጋሞ ምድር ጠብና አለማግባባት፤ ቂምና ቁርሾ የሚወገዱባቸው ጠንካራ ባህላዊ እሴቶች አሉ። የጋሞ ብሄረሰቦች ችግሮችን በባህላዊ መንገድ የመፍታት የቆየ ልምዳቸውን ጥቅም ላይ እያዋሉ ማህበራዊ መስተጋብራቸውን አጠናክረው የሚኖሩ ህዝቦች ናቸው። ልጆቻቸው ከማህበረሰቡ እሴቶች እንዳያፈነግጡ በአባቶች ምክርና ተግሳጽ ተኮትኩተው ስለሚያድጉ ለባህላዊ እሴቶች ተገዢዎች ናቸው፤ ታላላቆቻቸውንና አባቶቻቸውን ያከብራሉ፤ የሽማግሌዎችን ቃል ያደምጣሉ።

በጋሞ ምድር ማህበራዊ ግጭቶች በ‹‹ዱቡሻ›› እየታከሙ አፋጣኝ ፈውስ እንዲያገኙ ስለሚደረግ ለጸብ የተመዘዙ ሰይፎች ወደ አፎታቸው ለመግባት አይዘገዩም። እሳት በጭብጥ ለምለም ሳር ይጠፋል። የበደለና የማህበረሰቡን ወግና ሥርዓት የጣሰ በሽማግሌዎች ይወቀሳል። የተበደለ ይካሳል። አሻፈረኝ ብሎ ከማህበረሰቡ ባህላዊ እሴቶች ያፈነገጠም ይገለላል።

የጋሞ ማህብረሰብ ለማህበራዊ እሴቶቹ ያለውን ታማኝነት በተግባር ያሳየባቸውን አጋጣሚዎች ብናስታውስ፤ ለምሳሌ በ2011 ዓ.ም በቡራዩ ከተማ በጋሞ ተወላጆች ላይ የተፈጸመውን ጥቃት ተከትሎ የተወሰኑ ወጣቶች በቂም ተነሳስተው በአርባምንጭ ከተማ በሌሎች ላይ ጉዳት ሊያደርሱ በተነሱ ጊዜ የሀገር ሽማግሌዎች እንደ ባህላቸው በእጃቸው እርጥብ ሳር ጨብጠው እየተማጸኑ ማስቆሟቸው የሚረሳ አይደለም።

ጋሞዎች ሁልጊዜም ከአምባጓሮ ይልቅ ችግሮችን በንግግርና በውይይት የመፍታት ልምድ ያላቸው መሆኑን የማህበረሰቡ ነዋሪዎችና የሀገር ሽማግሌዎች ይናገራሉ።

በዛሬው የሀገርኛ አምዳችን ‹‹መተዳደሪያ የእርሻ መሬታችሁ ለልማት ስለሚፈለግ እንድትለቁ›› በመባላቸው ምክንያት ቅሬታ የገባቸው የአርባ ምንጭ አካባቢ አርሶ አደሮችን አቤቱታ ለፌዴራል መንግሥት ለማሰማት አዲስ አበባ ከመጡ የጋሞ አባቶች ጋር ቆይታ አድርገናል። ትኩረታችን ይዘው ስለመጡት አቤቱታ ሳይሆን ችግሮችን በሀገር ወግና ባህል መሰረት ለመፍታት በሚያደርጉት ጥረት ላይ ነውና በዚሁ ዙሪያ ከእነሱ ጋር ቆይታ አድርገናል።

ሽማግሌዎቹ በአካባቢው መስተዳድርና በአርሶ አደር ልጆች መካከል የተፈጠረው አለመግባባት ወደ መጥፎ ሁኔታ እንዳያመራ በጉዳዩ ዙሪያ ከሚመለከታቸው ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊዎች ጋር በመምከር ችግሩን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት አስበው የመጡ ናቸው። የጋሞ አባቶች ሁልጊዜ ችግሮችን በሰላማዊ መንገድ እንዲፈቱ የሚያስገድዳቸው ባህላዊ እሴታቸው ነው። አሁን ኢትዮጵያ አገራዊ ምክክርና መግባባት ለማደረግ እየተዘጋጀች ባለችበት በዚህ ሰዓት ከጋሞ አባቶች ምን ተሞክሮ ልትወስድ እንደሚገባት ጽሁፉን ካነበብን በኋላ የምናገኘው ቁም ነገር ይኖራል።

አቶ ካዎ ሙሉጌታ ከጋሞ አባቶቸ አንዱ ናቸው። በተለያዩ ሽምግልናዎች ላይ ተሳትፈው በርካታ ማህበራዊ ችግሮችን ፈትተዋል። በአንድ ወቅት በቡራዩ ከተማ በሚኖሩ የጋሞ ተወላጆች ላይ የተፈጸመውን ጥቃት ተከትሎ በአርባምንጭ ከተማ የሚገኙ ወጣቶች የበቀል ጥቃት ለመፈጸም ሲሞክሩ እንደማህበረሰቡ ባህል እርጥብ ሳር በእጃቸው ይዘው የወጣቶቹን ቁጣ ካቀዘቀዙት ሽማግሌዎች መካከል አንዱ ናቸው። ዛሬም ለሽምግልና አዲስ አበባ መጥተው አግኝተናቸዋል።

የጋሞ ማህበረሰብ እና ሽማግሌዎቻቸው ስምና ወርቅ ናቸው፤ መደማመጥና መከባበር የማህበረሰቡ መገለጫ ነው ይላሉ። በተለይም ወጣቶች ለሽማግሌዎች ቃልና ለባህላዊ እሴታቸው ታማኝ ናቸው። በሽማግሌዎች ምክርና በማህበረሰቡ ወግና ሥርዓት ተኮትኩተው ስለሚያድጉ ከባህላዊው ወግና ሥርዓት አያፈነግጡም። ስለሆነም ለጥፋት ሊዘረጉ የሚሞክሩ የጋሞ ማህበረሰብ እጆች በሽማግሌዎች ተግሳጽ በፍጥነት ይሰበሰባሉ ይላሉ አቶ ካዎ።

ይህን ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ምሳሌ የሆነ ገድል የፈጸሙ የጋሞ አባቶችም በአማራ፣ በኦሮሚያና በሌሎችም የደቡብ ዞኖች እየተገኙ ልምዳቸውን አካፍለዋል። አቶ ካዎም የጋሞ አባቶችን በመወከል በተለያዩ ክልሎች እየተጋበዙ ስለጋሞ አባቶች ልምድና ተሞክሮ አካፍለዋል።

እርሳቸው እንደሚሉት የጋሞ ብሄረሰብ የራሱ ባህልና ማንነት አለው ። ሰው ወዳድና አቃፊ ነው። እርስ በእርስም ይሁን ከሌሎች ብሄረሰቦች ጋር ግጭቶች ሲፈጠሩ ጸብ የሚያበርድባቸው ባህላዊ ሥርዓቶች አሉት። በብሄረሰቡ ዘንድ እርጥብ ሳር፣ ጋሻና ጦር ትርጉም አላቸው። ሰዎች ሲጣሉ ሽማግሌዎች እርጥብ ሳር ይዘው መሃል ይገባሉ፤ ጸቡ ደም የፈሰሰበት ወይም ህይወት የጠፋበት ከሆነም ጋሻና ጦር ይዘው በመንበርከክ ጸቡ እንዲቆምና ደም እንዳይፈስ ይማጸናሉ። እናቶችም ተንበርክከው ጡታቸውን በማውጣት በጠባችሁት ጡት እያሉ ጸብ እንዲበርድ ያደርጋሉ። በዚህ ወቅት ማንም ሰው ለጸብ መጋበዝ የለበትም። ሁሉም በያለበት ይቆማል።

በድንበር ምክንያት በብሄረሰብና በጎሳዎች መካከል ቡድናዊ ግጭት ሲፈጠር /አገትሳ/ የሚባል መልእክተኛ ይላካል። አገትሳው /መልእክተኛው/ ህብረተሰቡን ያገለግላል ተብሎ ከሚታመን ቤተሰብ የሚመረጥ ነው። ግጭት ከመከሰቱ በፊት ሁኔታው በውይይት እንዲፈታ በዳይና ተበዳዮች ችግሩን እንዲፈቱ ያቀራርባል። ጉዳዩን የሚመለከቱ ሽማግሌዎች ከዚህም ከዚያም ወገን ተውጣጥተው ይሰየማሉ። ሽማግሌዎች በባህሉ መሰረት የበዳይና የተበዳይን ሀሳቦች አዳምጠው ተገቢውን ፍርድ ይሰጣሉ። የተበደለ ይካሳል የበደለም ይወቀሳል ወይም ይቀጣል።

በግጭቱ ወቅት የሰው ህይወት ቢጠፋ እንኳ እርቅ ከተፈጸመ በኋላ ጉዳዩ ዳግም አይነሳም። ሰዎች ያለፈውን በደል እረስተው በሰላም እንዲኖሩ ይደረጋል። የማህበረሰቡን ደንብና ሥርዓት መተላለፍና የሽማግሌዎችን ሀሳብ አለመቀበል በትውልድ ላይ የሚያስከትለው ርግማንና ቁጣ እንዳለ ስለሚታመን ሁሉም ለሥርዓቱ ይገዛል። ከሽማግሌ ዳኝነት ወጥቶ በራሱ ስልጣን ርምጃ ሊወስድ የሚነሳ ሰው ቢኖር እንኳ የራሱ የቅርብ ዘመዶች በሽማግሌ ርግማን ዘራችንን ታስጨርሳለህ በሚል ሀሳቡን አይቀበሉትም። ከዚህም ባሻገር ከአካባቢው ማህበረሰብ ውግዘት ስለሚደረስበት ይገለላል ይላሉ እንግዶቻችን።

ባለፈው በቡራዩ የጋሞ ተወላጆች ላይ የተፈጸመውን ጥቃት ለመበቀል የተደረገውን ሙከራ ማስቆም የተቻለውም ወጣቱ የአባቶቹን ምክርና ተግሳጽ ስለሚሰማና የሥርዓቱ ተገዢ ስለሆነ ነው።

የጋሞ ማህበረሰብ ጥብቅ ባህል እንዳለው የሚናገሩት አቶ ካዎ፤ ለእርቅና ለሰላም የተዘጋጀ ሥነልቦና የገነባ ነው ይላሉ። እርስ በእርስ በመገፋፋትና በመጠላላት ሀገር ሊያድግ አይችልም፤ ኢትዮጵያ ማደግ የምትችለው ልጆች የአባቶቻቸውን ቃል እየሰሙ ከጥፋት መንገድ ሲታቀቡና ሰላም በማስፈን ሰርተው መኖር ሲችሉ ነው።

ባህላዊ እሴቶቻችን የሀገርን ሰላምና ደህንነት ከማረጋገጥ አንጻር ከዩኒቨርሲቲዎች ያልተናነሰ ትውልድን የመገንባት አቅም አላቸው። የሀገሩን ሰርዶ በሀገሩ በሬ እንደሚባለው ወጣቱ ሀገሩን ከጠላት ለመከላከል ወደ ጦር ግንባር እንደሚዘምት ሁሉ የአባቶቹን ባህላዊ እሴቶችን በማክበርም ሰላሙን አስፍኖ ሀገሩን ከውድቀት መታደግ ይኖርበታል ብለዋል።

የጋሞ አካባቢ ወጣቶች ለባህላቸው ተገዢ መሆናቸው የአካባቢው ሰላም እንዳይደፈርስ አድርጓል፤ ሌሎችም ከዚህ ተምረው በየአካባቢያቸው የሀገር ሽማግሌዎችን ምክር ቢቀበሉ የኢትዮጵያን ሰላም ማረጋገጥ ይችላሉ። ሰላም ከሌለ አርሶ መብላት፣ አግብቶ መውለድ፣ መማርና መበልጸግ አይኖርም ያሉት አቶ ካዎ፤ እንደ ጋሞ ህዝብ በፍቅር፣ በሰላምና በመከባበር የሚኖር ማህበረሰብ መገንባት ሰላምን ለማስፈን ትልቅ ፋይዳ አለው ብለዋል።

በየብሄረሰቡ ጠቃሚ እሴቶች እንዳሉ የሚናገሩት አቶ ካዎ፤ ሁሉም ተሞክሮዎቻቸውን ቢለዋወጡ ለሀገር ሰላምና ግንባታ ጠቃሚ ይሆናል ብለዋል። አቶ ካዎ ከሌሎች የጋሞ አባቶች ጋር በመሆን ቡራዩ ድረስ በመሄድ እርቅና ሰላም እንዲወርድ አድርገዋል፤ በአማራ ክልል ጎጃምና ጎንደር በመሄድ ልምድና ተሞክሯቸውን አስተዋውቀዋል። በጉጂና ቡርጂ ብሄረሰቦች መካከል ግጭት ሲፈጠር ቦታው ድረስ በመሄድ አስታርቀዋል። ከየአካባቢው የተውጣጡ የሀገር ሽማግሌዎች በጋሞ ባህልና ሥርዓት ላይ ኮንፈረንስ አካሂደው ጠቃሚ ልምዶችን አግኝተዋል። የሀገር ሽማግሌዎች ብቻ ሳይሆኑ ወጣቶችም የጋሞን ማህበረሰብ የመከባበር ባህል ቀረብ ብለው ቢጎበኙ በርካታ ትምህርቶችን ሊያገኙበት ይችላሉ ብለዋል።

በጋሞ አካባቢ የሚኖሩ ወጣቶች እርስ በእርሳቸው ጸያፍ ስድቦችን ሲሰዳደቡ ቢሰሙ የአምስት መቶ ብር (500) ብር ቅጣት ተጥሎባቸዋል። መሰዳደብ ባህላችን እንዳልሆነ እንነግራቸዋለን። ወጣቶች በሥነምግባር እንዲታነጹ ሁሉም ቦታ የሚገኙ የሀገር ሽማግሌዎች የራሳቸውን አስተዋጽኦ ቢያበረክቱ የሀገርን ሰላም ለማረጋገጥ ትልቅ ጥቅም አለው።

አቶ ቦኖ ቦሻ የአርሶ አደሮችን ቅሬታ ለማሰማት ለሚመከተው አካል ለማሳወቅ የመጡ ሌላው የጋሞ አባት ናቸው። እርሳቸው እንደሚሉት ቅሬታን በንግግር መፍታት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ባህላቸው ነው። በጋሞ ባህል የወላጆቹንና የሽማግሌዎችን ምክር የማይቀበል ልጅ እንደልጅ አይታይም።

ወጣቶች ወደ ጥፋት እንዳይገቡ የሚያደርጋቸው የሽማግሌዎችን ቃል ስለሚሰሙ ነው። ማህበረሰቡ በ‹‹ዱቡሻ›› ሥርዓት እየተገራ ስለሚኖር መልካም እንጂ መጥፎ ነገርን ለማድረግ አይነሳሳም። “የጋሞ ባህል ከወንጌል ቃል ጋር ይቀራረባል” የሚሉት አቶ ቦኖ፤ ሰዎች ቂም ይዘው እንዲያድሩ አይፈለግም፤ የተኮራረፉ ሰዎች ካሉም ውለው ሳያድሩ እንዲታረቁ ይደረጋል ይላሉ።

አባቶች ችግሮች በሰላማዊ መንገድ እንዲፈቱ ያስተምራሉ፤ ይመክራሉ። ልጆችን የሚያስተምሩት ባህልን ከወንጌል ቃል ጋር እያስተሳሰሩ ስለሆነ ክፉ ነገር ለመሥራት የሚነሳሳ ሰው አይኖርም።

የጋሞ አባቶች በልጆቻቻው ኩራት የሚሰማቸው ናቸው፤ ወጣቶች ከቃላቸው አይወጡም፤ የሚሏቸውን ሰምተው ይተገብራሉ። ወጣቶች የሽማግሌዎችን ቃል በመስማታቸው እራሳቸውን ከጥፋት ታድገው ለአባቶቻቸው ሞገስ ሆነዋቸዋል። በተለያዩ መድረኮች የጋሞ አባቶች መልካም ሥራ እየተባለ ለመነገር የበቃው ማህበረሰቡ የሀገር ሽማግሌዎችን ቃል ስላከበረ ነው።

ሁሉም ብሄረሰብ በየአካባቢው ጥሩ ጥሩ ባህሎችና ባህሉን የሚያስፈጽሙ የሀገር ሽማግሌዎች አሉት። መኖሩ ብቻውን ትርጉም ላይኖረው ይችላል፤ ዋናው ቁም ነገር እሴቱን እንደ አስፈላጊነቱ ጥቅም ላይ ማዋል ነው።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይ አሕመድ ስለጋሞ የሀገር ሽማግሌዎች ገድል በተለያዩ መድረኮች ላይ ሲያነሱ ይሰማል። የጋሞ አባቶች ሊወደሱ የቻሉት በትውልድና በባህል መካከል ክፍተት እንዳይፈጠር አስቀድመው በመሥራታቸው ምክንያት የሚታዘዛቸው ወጣት ስላገኙ ነው።

ሁሉም ማህበረሰብ በየአካባቢው በአዲሱ ትውልድና በባህል መካከል ያለውን ክፍተት በማጥበብ ወጣቱ የመቻቻልና የአብሮነት እሴቱን እንዲጠብቅ ማድረግ ይኖርበታል። ለዚህም የሀገር ሽማግሌዎች ሚናቸውን ሊወጡ ይገባል።

መንግሥትም እንዲህ አይነት እሴቶች እንዲጎለብቱ እገዛ ማድረግ ይጠበቅበታል። እንዲህ አይነቶቹ እሴቶቻችን የታሰበውን ሀገራዊ ምክክርና መግባባት እውን ለማድረግ እገዛ የሚያደርጉ ናቸው። ወደ ሰላም ጎዳና የሚያመጡንን ባህሎቻችንን ማጎልበትና በሀገራዊ ምክክሩና ማግባባቱ የራሳቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ማድረግ ያስፈልጋል።

‹‹ዱቡሻ›› የጋሞ ብሄረሰብ የእርቅና የሰላም ባህልም ሊካሄድ በታሰበው አገራዊ የምክክርና የመግባባት መድረክ ላይ የራሱን ድርሻ እንዲያበረክት የጋሞ አባቶችን ወደ መድረኩ መጋበዝ ያስፈልጋል። የጋሞ ባህልን የጋሞ ማህበረሰብ ብቻ ሳይሆን መላው ኢትዮጵያውያን ቢጠቀሙበት ሰላምና ፍቅርን ያተርፉበታል እንጂ አይጎዱበትም።

ቱባው ባህላዊ እሴቶቻችን የሆነው ዱቡሻ ለዘለአለምይኑር። አሜን!!!

መዝናኛ

# የብዕር ጠብታ

## የትዝታ ገጾች

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

ከአስር አመት በኋላ መኝታ ክፍሌ አልጋ ውስጥ ያስቀመጥኩትን የወረቀት ፋይል አገላብጣለሁ። ዩኒቨርሲቲ እያለሁ የማነባቸውን መጽሐፍቶች፣ የተማርኩባቸውን አንዳንድ ደብተሮች እያየሁ የትዝታ አለንጋ ገረፈኝ። ከዩኒቨርሲቲ ከወጣሁ ጀምሮ እጄን ወደ አልጋዬ ሰድጄ አላውቅም። ዛሬ ምን ወደዛ እንደሰደደኝ አላውቅም፤ ትዝታዎቼ በአእምሮዬ ውስጥ እንጂ እንዲህ አካል ለብሰው ወረቀት ላይ አገኛቸዋለሁ ብዬ አልገመትኩም ነበር። አልጋዬ ስር ባስቀመጥኩት ትናንቴ ወደ ተውኩት አምና ተሰደድኩ።

የትዝታ ተጠቂ ነኝ፤ ትናንትና ምንም ይሁን ከነግሳንግሱ ይናፍቀኛል። ነገ የትናንትን ያህል ናፍቆኝ አያውቅም። ዘንድሮ ያምናን ያህል ብርቅ ሆኖብኝ አያውቅም። በእኔ ሕይወት ውስጥ ዛሬ ነገ ሲሆን ሁሉም ትዝታ ነው። ከሙዓለ ሕፃናት እስከ አሁን ድረስ ያለው ትናንት፣ ያለው አምና፣ ያለው ድሮ ናፍቆቴ ነው። ትናንትን አንቆ መግደል አቅቶኛል።

ብዙ ነገሮችን አየሁ፤ የረሳኋቸውን ብዙ ነገሮች አስታወስኩ። ደብተሬ ላይ የብዙ ጓደኞቼ የእጅ ጽሑፍ ነበር። ክፍል ውስጥ ማድመጥ እንጂ መጻፍ አልወድም ነበር፤ ለዚህም ክፍል ውስጥ እኔ ደብተር ላይ ያልጻፈ አንድም ተማሪ አልነበረም።

ትናንትናዬን ገለጥኩት፤ ዛሬም ድረስ የማይረሳኝን የመክሊትን የእጅ ጽሑፍ ደረስኩበት። መክሊት የክፍላችን ብቻ አይደለችም፤ የዩኒቨርሲቲያችን ብቸኛ ቆንጆ ተማሪ ነበረች። ዛሬም ድረስ የእሷን ዓይነት ቆንጆ ሴት አላየሁም። ድሮዊንግ አስተማሪያችን በእሷ ምክንያት ‹ሔፍ› እስከሰጠኝ ጊዜ ድረስ ተለያይተን አናውቅም ነበር።

አይ ቲቸር ሞገስ፤ ቲቸር ሞገስ ድሮዊንግ አስተማሪያችን ነው፤ ክፍል እንደገባ የመጀመሪያ ሥራው ወዳለችበት ተራምዶ አጠገቧ መቆም ነው። ከዚያ በኋላ ነው ጥቁር ሰሌዳው ላይ የሆነ ነገር ስሎ የሚያስተምረን። ከእኔ ኋላ ስለምትቀመጥ አጠገቧ ሲቆም ጥላው ያርፍብኛል። ዛሬም ድረስ የሚጠርነኝ ሽቶው ይሸተኛል። ሰማይ የተደፋብኝ ያህል ክብድ ይለኛል። ወንድነቱ ነፍሴ ላይ ያርፋል። ሰው እንዴት ያንን ያህል ይገዝፋል? ሳይናገር፣ ሳያወራ፣ ቃል ከአፉ ሳያወጣ የኔን ነፍስ ያስጨንቃታል።

እሱ ጎልያድን እኔ ደግሞ ዳዊትን ሆነን እዚያ ስፍራ ለአንድ አመት ተሰቃይቻለሁ። ከአጠገቤ እብስ ሲል እንደ ዳዊት በጠጠር ያባረርኩት ነበር የሚመስለኝ። በነጋታው አጠገቤ ጥላው አርፎብኝ ሳየው ጎልያድ ፊት እንደ ቆመው ኮሳሳው ዳዊት እኮስሳለሁ።

ቲቸር ሞገስ የመክሊትን ስም ሳይጠራ አስተምሮን አያውቅም። ዛሬም ድረስ ያልገባኝ ነገር የሴት ስም ለአንድ ድሮዊንግ ምሳሌ ሆኖ መቅረቡ ነው። አመት ሲያስተምረን ከመክሊት ስም ሌላ ምሳሌ ተጠቅሞ አያውቅም። እኛ ክፍል ኤክስና ዋይ የሚያርፉት በድሮዊንግ ክላስ በመክሊት ስም ነው። ኤክስና ዋይ ነፍስ ቢኖራቸው ኖሮ መክሊትን የሚያመሰግኑ ይመስለኛል። ክላስ ውስጥ በእሷ ምክንያት ለሰባት ልጆች ‹ሔፍ› ሰጥቷል.፤ ከዚያ ውስጥ አንዱ እኔ ነኝ። በአንድ ቆንጆ ሴት ምክንያት ምንም የማናውቅ የሰባት ወንዶች ህልም መደናቀፉ ዛሬም ድረስ ያናድደኛል። ቲቸር ሞገስ ለምን መምህር እንደሆነ አላውቅም።

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ መክሊትን ፈራኋት፤ ግዝት እንዳለበት ሰው በመቶ ሜትር ነበር የምርቃት። እስከተመረቅንበት ጊዜ ድረስ አውርቻት አላውቅም። የምርቃታችን ጊዜ ከአዳራሽ ስወጣ ጠብቃ አንድ ነገር አለች፤ ‹ከእንግዲህ እኮ አንገናኝም፣ ነገ ለእኔና ለአንተ ሌላ ቀን ነው፤ ከአንተ ጋ አንድ ማስታወሻ እንዲኖረኝ እፈልጋለሁ አለችኝ።

ዝም ብዬ ፊቷ ቆምኩኝ፤ ያ ቀን ከረጅም ጊዜ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ፊቷ የቆምኩበት ቀን ነው። በደንብ አየኋት፤ እንደ ዛ ቀን ውብ ሆና አይቻት አላውቅም። ፊቷ ላይ ውበቷን ያደመቁ ብዙ ዓይነት ቀለሞች ይታዩኛል። ቅንድቧ በቀጭን ተቀንድቧል፣ ዓይኖቿ ዙሪያ ገባውን ተኩለዋል። ጉንጮቿ በወዛማ ቀለም ልመዋል። ከንፈሯ እንደምትወደው በማውቀው፣ ሰማይ ቤት ድረስ ይዛው በምትሄደው ቀይ ቀለም ደምቋል። በዚህ ሁሉ ውስጥ ዓይኖቿ ይስቃሉ፣ ጠንበለል አካሏ ይቁነጠነጣል።

‹ነገ ሲሆን ሁሉም ሌላ ነው…የአሁን ማለዳዎች በኋላ የሚመሹ ናቸው። ነገ በሚደበዝዙ አጋጣሚዎች ልትለያት አንድ ቀን የቀረህን ጓደኛህን አታሳዝናት› ስትል ሰማኋት።

ልቤ አራራልህ አለኝ። በሕይወቴ ሁሉም ቦታ ያለች ሴት ሆና ግን ጨከንኩባት። የነፍሴ ቦታ ቢታይ..የልቤ ስፍራ ቢፈተሽ እሷ ብቻ ናት ግን ፊት ነሳኋት።

ዓይኖቿ ይማጸኑኛል…ዓይኖቼ ይሸሹዋታል።

ከየት እንዳመጣሁት የማላውቀው እንቢ ልላት የሚያስችል ብዙ ኃይል ነበረኝ። ዕድሜ ለቲቸር ሞገስ እንደ አራስ ነበር እንድፈራት አድርጎኛል። በዚያ በመጨረሻ ሰዓት አንድ ፎቶ እንነሳ ብላ ከነጋዋ ፊቴ ስትቆም ትቻት ነበር የሄድኩት። ያ ቀን ሁሌም ይቆጨኛል። ምነው እሺ ባልኳት ስል አስባለሁ። ዛሬ ላይ ከእሷ ይልቅ እኔ ነበርኩ ያ ፎቶ የሚያስፈልገኝ እላለሁ። ከእሷ ጋር ለመታረቅ ያ ቀን ትክክለኛ ጊዜ ነበር። ያን ያህል ለምን እንደጠላኋት አላውቅም። በጣም የሚገርመው ደግሞ በሸሸኋት በነዛ ሁሉ ቀናት ውስጥ ልታናግረኝ ስትከተለኝ እንደነበረኝ አስታውሳለሁ።

አሁን ላይ ልቤ ይቅር ብሏት ቢሆን ኖሮ እላለሁ። አሁን ላይ አንድ አይደለም ከእሷ ጋር ለቁጥር የሚታክቱ ፎቶዎች ኖረውኝ ቢሆን እላለሁ። በተለያየንባቸው አስር አመታት ውስጥ ሳላስባት የቀረሁበት ጊዜ አልነበረም። እሷም ይሄን ስለምታውቅ ነው መሰለኝ ትናንትና ዛሬ አንድ ዓይነት አይደሉም ያለችኝ። ከሰው ልጅ ቀድሞ ሕይወት የገባት ሴት ትመስለኛለች።

ትናንት ላይ ሆና ዛሬዬን አይታልኛለች። ባሳለፍኩት አስር አመታት ውስጥ ነፍሴ እንደ እሷ የተራበችው ሰው የለም። እኔም በእሷ የተራቆትኩትን ያህል በምንም አልተራቆትኩም። አሁን የት እንዳለች አላውቅም፤ ይሄ ሁሉ ዘመን አልፎ እንኳን ከውስጤ አልደበዘዘችም፤ ፊቴ ቆማ አንድ ፎቶ እንነሳ እንዳለችኝ እኔም አንድ ቀን ፊቷ ቆሜ እባክሽ ፎቶ እንነሳ የምልበት ቀን ይመጣል እላለሁ።

ምድር ላይ ዳግም እኔና እሷ እዛ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ፣ እዛ ክፍል፣ እዛ አዳራሽ በር ላይ ብንፈጠር እላለሁ። እዛ ክፍል በቲቸር ሞገስ ብንማር እላለሁ። ስለ እሷ የማይሆን ነገር አስባለሁ።.

# ዓለም አቀፍ



## ሩሲያ እና ዩክሬን የሰላም ድርድራቸውን በኦንላይን ሊቀጥሉ ነው

<u>አዲስ አበባ</u> ፦ ሩሲያ እና ዩክሬን የሰላም ድርድራቸውን በቀጥታ (በኦንላይን) ሊቀጥሉ ነው።

የዩክሬን ተደራዳሪ ዴቪድ አራካሚያ ሁለቱ ሃገራት በቱርክ ስኬታማ ውይይት ማድረጋቸውን አስታውሰው፤ በዛሬው እለት በኦንላይን ቀጣይ ድርድራቸውን ያካሂዳሉ ብለዋል።

አያይዘውም ዩክሬን የሁለቱ ሃገራት መሪዎች ተገናኝተው የሚደራደሩበትን ሃገር በተመለከተ ሃሳብ ማቅረቧን አስታውቀዋል።

ይሁን እንጂ ከሩሲያ በኩል ሃገራቱ በሚገቡት የስምምነት ረቂቅ ላይ ተጨማሪ ስራ መስራት አለበት የሚል ምላሽ መሰጠቱን ጠቁመዋል።

በሌላ በኩል ሩሲያ በማሪፑል ከትናንት ጀምሮ የሚተገበር የተኩስ አቁም ይፋ አድርጋለች።

የተኩስ አቁሙ ንጹሃንን ከጦርነት ቀጣናው ለማስወጣት እንደሚረዳ የሩሲያ መከላከያ ሚኒስቴር መግለጹን ሲ ጂ ቲ ኤን ዘግቧል።

## አሜሪካ የኢኮኖሚ እና ንግድ ጉዳዮችን ስፖስቲካ ፍጆታ ከማዋል እንድትቆጠብ ቻይና ጠየቀች

<u>አዲስ አበባ</u>፡- አሜሪካ በቻይና የኢኮኖሚ እና ንግድ ጉዳዮች ላይ ያላትን የተሳሳተ አቀራረብ በአስቸኳይ እንድታርም የቻይና ንግድ ሚኒስቴር አስጠነቀቀ፡፡

የቻይና ንግድ ሚኒስቴር ቻይና በምታደርጋቸው የንግድ እንቅስቃሴዎች ላይ ጫና በመፍጠር ኢኮኖሚዋን ለመጉዳት አሜሪካ ፖለቲካዊ ጫና እያሳደረች ነው ሲል ይከሳል፡፡

ሚኒስቴሩ አሜሪካ በቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት እና በመገናኛ ቁሳቁስ ሽያጭ ዘርፍ ላይ ተሰማርተው የሚገኙ “ቻይና ቴሌኮም አሜሪካስ” እና “ቻይና ሞባይል ኢንተርናሽናል ዩ ኤስ ኤ” የተሰኙትን የቻይና ኩባንያዎች ለብሔራዊ ደኅንነቴ ስጋት ናቸው ብላ መፈረጇን ሚኒስቴሩ ጠቁሟል፡፡

የቻይና ንግድ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ ሹ ጁቲንግ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ፤ አሜሪካ ኩባንያዎቹን በዚህ መልኩ መፈረጇ ፍጹም ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ገልጸዋል።

ቃል አቀባዩ ቻይና መብቷን ለማስከበርም አስፈላጊውን ሁሉ እርምጃ በቆራጥነት ትወስዳለች ማለታቸውን ሲ ጂ ቲ ኤን ዘግቧል።

# ስፖርት

# የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ቻምፒዮና ነገ ይጠናቀቃል

ቦጋስ አበበ

51ኛው የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ቻምፒዮና ካለፈው ሰኞ ጀምሮ በሐዋሳ ስቴድየም እየተካሄደ ዛሬ አምስተኛ ቀኑን ይዟል። ቻምፒዮናው ነገ በተለያዩ ርቀቶች በሚካሄዱ የፍጻሜ ውድድሮች ይጠናቀቃል። በቻምፒዮናው የመጀመሪያ ሁለት ቀናት ስድስት አዳዲስ ክብረወሰኖች መሰበራቸው በቀጣይ ቀናት ውድድሮችም በርካታ ክብረወሰኖች እንደሚሻሻሉ ተስፋ የሰጠ ቢሆንም እስከ ትናንት በተካሄዱ ውድድሮች አንድ ተጨማሪ ክብረወሰን ብቻ ነው መሻሻል የቻለው።

በቻምፒዮናው ሦስተኛ ቀን ውሎ ከአስር አመት በኋላ የወንዶች ዲስከስ ውርወራ ክብረወሰን ተሻሽሏል። በ2004 ዓ.ም አዲስ አበባ ላይ በመከላከያው አትሌት ምትኩ ጥላሁን 44.33 ሜትር ተይዞ የቆየው የኢትዮጵያ ክብረወሰን ዘንድሮ በሲዳማ ቡናው አትሌት ማሙሽ ታዬ ተሻሽሏል። አትሌቱ ክብረወሰኑን ያስመዘገበውም 45.09 ሜትር በመወርወር ነው። በዚህ ውድድር አትሌት ገበየሁ በእየሱስ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ 43.77 ሜትር በመወርወር ሁለተኛ ሆኖ ያጠነቀቀበትን ውጤት ሲያስመዘግብ አብዲሳ ገመቹ ከአዳማ ከተማ 42.85 ሜትር በመወርወር የነሐስ ሜዳሊያ አሸናፊ ሆኗል።

ምንም ክብረወሰን ባልተመዘገበበት የቻምፒዮናው አራተኛ ቀን ውሎ ትናንት የተወሰኑ የፍጻሜ ፉክክሮችን ተካሂደዋል። በተለይም በሦስት ሺ ሜትር መሰናክል በሁለቱም ጾታ የተካሄዱ ውድድሮች ትልቅ ትኩረት ያገኙ ሲሆን የርቀቱ የኢትዮጵያ ቻምፒዮኖችም ተለይተውበታል። በዚህም በሴቶች አትሌት ወርቅውሃ ጌታቸው ከመከላከያ በ09፡41.79 የርቀቱ ቻምፒዮን ስትሆን በወንዶች ሳሙኤል ፍሬው ከጥሩነሽ ዲባባ ማሰልጠኛ በ08:22:48 የኢትዮጵያ ቻምፒዮን መሆኑን አረጋግጧል።



በዘንድሮው የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ቻምፒዮና አዳዲስ ክለቦች ጠንካራ ተፎካካሪ በመሆን በርካታ ሜዳሊያዎችን እየሰበሰቡ ይገኛሉ፣

በሴቶች መካከል የተካሄደውን ውድድር መቅደስ አበበ ከአማራ ክልል 09:43:72 በማጠናቀቅ የብር ሜዳሊያ ስታጠልቅ፣ የሲዳማ ቡናዋ ዘርፌ ወንድማገኝ በ09:44:85 የነሐስ ሜዳሊያውን የግሏ አድርጋለች። በተመሳሳይ በወንዶች ቻምፒዮኑን ተከትሎ በመግባት ኃይለማርያም አማረ ከፌዴራል ማረሚያ 08፡24.53 ሁለተኛ ሆኖ ሲያጠናቅቅ፣ ታደሰ ታከለ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ 08፡26.01 ሦስተኛ በመሆን አጠናቋል።

ጥሩ ፉክክር እየተስተናገደባቸው በሚገኙት የሜዳ ተግባራት ፉክክሮች ርዝመት ዝላይ በወንዶች ትናንት ፍጻሜ ሲያገኝ፣ ኡመድ ኡኩኛ ከሲዳማ ቡና 7.47 ሜትር በመዝለል አሸናፊ ሆኗል። ድሪባ ግርማ ከመከላከያ 7.33 ሜትር በመዝለል ሁለተኛ ሲሆን በቀለ ጅሎ ከኦሮሚያ ክልል 7.29 ሜትር ዘሎ ሦስተኛ ሆኖ አጠናቋል። የከፍታ ዝላይ የወንዶች ውድድርም በጥሩነሽ ዲባባ ማሰልጠኛ አትሌት አበራ አለሙ አሸናፊነት ተፈጽሟል። አትሌቱ ቻምፒዮን የሆነው 4.10 ሜትር ከፍታ በመዝለል ነው። 4:00 ሜትር ከፍታ የዘለለው የመከላከያ አትሌት ሳምሶን በሻ ሁለተኛ ሆኖ ሲያጠናቅቅ፣ አበበ አይናለም ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ 3.90 ከፍታ በመዝለል ሦስተኛ ደረጃን ይዟል።

በቻምፒዮናው ሦስተኛ ቀን ውሎ ከትናንት በስቲያ ፍጻሜ ካገኙ ውድድሮች አንዱ በሆነው የሴቶች ምርኩዝ ዝላይ ውድድር የጥሩነሽ ዲባባ ማሰልጠኛ አትሌቶች የወርቅና የብር ሜዳሊያዎችን አሸንፈዋል። የነሐስ ሜዳሊያውን ማሸነፍ የቻለ አትሌት በሌለበት በዚህ ውድድር ሲፈን ሰለሞን 2.10 ሜትር ከፍታ በመዝለል የወርቁን ሜዳሊያ ስታሸንፍ ሜቲ ቤኩማ 2.00 ሜትር ከፍታ ዘላ የብሩን ሜዳሊያ ወስዳለች።

በተመሳሳይ የሴቶች ርዝመት ዝላይ ውድድር ኪሩ ኢማን ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ 5.75 ሜትር በመዝለል ስታሸንፍ፣ ማሬዋፒዶ ከመከላከያ በ5.68 ሜትር ተከታዩን ደረጃ ይዛ ፈጽማለች። አርያት ዴቪድ ከኢትዮጵያ ወጣቶች ስፖርት አካዳሚ 5.68 ሜትር ሦስተኛ ሆናለች።

በ110 ሜትር መሰናክል ወንዶች ማረሰ ተስፋዬ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ 14.06 ሰዓት የርቀቱ የ2014 ዓ.ም ቻምፒዮን ሲሆን ኬሪዮን ሞርቴ ከኦሮሚያ ክልል 14.43 ሰዓት፣ ሮድ ቾል ከጥሩነሽ ዲባባ ማሰልጠኛ በ14.76 ሰዓት ሁለተኛና ሦስተኛ ደረጃን ይዘው አጠናቀዋል። በቻምፒዮናው ያለፉት አራት ቀናት ውሎዎች እንደወትሮው በርካታ ውድድሮችን ማሸነፍ ያልቻሉት ኦሮሚያ ክልልና መከላከያ በመቶ ሜትር ሴቶች መሰናክል ውድድር ሁሉንም ሜዳሊያዎች አሸንፈዋል።

በተለይም ኦሮሚያ ክልል ውድድሩን 14.08 ሰዓት ቀዳሚ ሆና ባጠናቀቀችው ሂርጳ ድርባ የወርቅ ሜዳሊያውን ሲወስድ የብር ሜዳሊያውንም 14:17 በሆነ ሰዓት ባጠናቀቀችው አለሚቱ አሰፋ አማካኝነት የግሉ ማድረግ ችሏል። ቀሪውን የነሐስ ሜዳሊያም ምህረት አሻሞ 14.28 በሆነ ሰዓት አጠናቃ ለመከላከያ አስመዝግባለች።

ቻምፒዮናው ነገ የሚጠናቀቅ ቢሆንም በዛሬው ዕለት ከማለዳ ጀምሮ በሁለቱም ጾታ የሚካሄዱ የሃያ ኪሎ ሜትር ርምጃ ውድድሮችን ጨምሮ በርካታ የሜዳ ተግባራትና አጭር ርቀት የፍጻሜ ፉክክሮችን እንደሚያስተናግድ ከወጣው መርሃግብር መረዳት ተችሏል።


## የጨረታ ማስታወቂያ

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ለሰጠው ብድር በዋስትና የያዛቸውን ቤቶች በአዋጅ ቁጥር 97/90 በተሰጠው ስልጣን መሰረት በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ መሸጥ ይፈልጋል ፡፡

| ተ.ቁ | የተበዳሪው ስም | አበዳሪ ቅርንጫፍ | የንብረቱ አይነት ፤ስፋት እና የሚገኝበት ቦታ | የጨረታ መነሻ ዋጋ | የጨረታው ደረጃ | ጨረታው የሚካሄድበት ቀን | ጨረታው የሚካሄድበት ሰዓት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | ጦና ደሳለኝ | ሻሸመኔ | ሻሸመኔ ከተማ ቀበሌ 10 የሚገኝ የመኖሪያ ቤት | 733.911.03 | 2ኛ | ሚያዝያ 30 ቀን 2014 ዓ.ም | ከ4 - 6 ሰዓት |

**ማሳሰቢያ፡-**

1. ተጫራቾች የጨረታ መነሻ ዋጋውን /4ኛ በባንክ በተረጋገጠ የክፍያ ሰነድ (CPO) በማቅረብ ወይም በጥሬ ገንዘብ በማስያዝ መወዳደር ይችላሉ ፡፡
2. የጨረታው አሸናፊ ቀሪውን ገንዘብ በ15 (አስራ አምስት ) ቀናት ውስጥ አጠናቆ መክፈል ይኖርበታል። በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ክያፍው ባይፈጸም ግን የሐራጁ ውጤት ተሰርዞ ያስያዘው ገንዘብ ወይም CPO አይመለስለትም ፡፡
3. ንብረቱ በገዢው ስም እንዲዛወር ባንኩ ለሚመለከተው መንግስታዊ አካል ደብዳቤ ይጽፋል። የባንኩን የብድር መመሪያ መስፈርት ለሚያሟላ ገዢ ባንኩ ከፊል ብድር ሊያመቻች ይችላል ፡፡
4. ውዝፍ የሊዝ ክፍያ፤ተጨማሪ እሴት ታክስ እና ሌሎች ገዥ እንዲከፍላቸው በህግ የተወሰኑ ክፍያዎችን ገዢ ይከፍላል ፡፡
5. ጨረታው ንብረቱ በሚገኝበት ከተማ እና ቦታ ይካሄዳል ፡፡
6. ባንኩ የተሻለ አማራጭ ካገኘ በጨረታው አይገደድም ::
7. ስለ ንብረቱ እና የሺያጭ ሁኔታው ዝርዝር ማብራሪያ ከተፈለገ በስ.ቁ. 04611o3382 ወይም በ 0911387237 ደውሎ መጠየቅ ይቻላል፡፡

**የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሻሸመኔ ዲስትሪክት**



## የጨረታ ማስታወቂያ/04

በጉራጌ ዞን ቸሀ ወረዳ ፋይናንስ ጽ/ቤት በቸ/ወ/ሴ/መ/ቤቶች የተሸከርካሪ ወይም ሞተር ሳይክል ግዥ መግዛት ይፈልጋል፡፡

1. በየንግድ ዘርፉ የተሰማራችሁ ተወዳዳሪዎች የዘመኑ ግብር የከፈላችሁ የታደሰ ንግድ ፈቃድና የምዝገባ ምስክር ወረቀት የቫት ተመዝጋቢ መሆናችሁ ማስረጃ ማቅረብ የምትችሉና ከዚህ በፊት በጨረታ ያልታገዳችሁ፤
2. ተጫራቾች ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ዘወትር በሥራ ሰዓት የጨረታውን ሰነድ ቸሀ ወረዳ ፋይናንስ ጽ/ቤት ቢሮ ቁጥር 7 በመቅረብ የማይመለስ ብር 100 አንድ መቶ ብር/ በመክፈል መግባት የምትችሉ መሆኑ፤
3. ተጫራቾች የጨረታ ዶክመንታችሁ ላይ በእያንዳንዱ ገጽ ላይ የድርጅቱ ማህተምና ፊርማ በማድረግ ከላይ በተራ ቁጥር 1 ላይ የተዘረዘሩ ማስረጃዎች ኦርጅናል 1 ሰነድና ኮፒ 2 በተለያዩ በታሸገ ፖስታዎች በማድረግ ለጨረታ በተዘጋጀው ሳጥን ማስገባት፡አለባችሁ፡፡
4. ተጫራቾች ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በተከታታይ 15/አስራ አምስት / የሥራ ቀናት አየር ላይ ይውላል እስከዚያ ድረስ የጨረታ ዶክመንታችሁን ማስገባት ይኖርባችኋል። ጨረታው የሚያበቃው የመጨረሻው ከቀኑ 8፡00 /ስምንት-ሰዓት/ሲሆን የሚከፈተው በዚሁ ቀን ከቀኑ 8፡30 ስምንት ተኩል/ተጫራቾችወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ሲሆን ባይገኙም ጨረታውን ለመክፈት የሚያግድ የሌለ መሆኑን እየገለጽን በአል/ቅዳሜና እሁድ ከሆነ የሚቀጥለው የሥራ ቀን ይተላለፋል፡፡
5. ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ የሚሆን ገንዘብ በባንክ በተረጋገጠ ሲፒኦ 10000(አስር ሺ ብር /በቴክኒካል ዶክመንት ማስገባት አለባችሁ፡፡
6. መ/ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታው ሙሉ በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

ለበለጠ መረጃ 0113310812/0113310254

**በደብ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/በጉራጌ ዞን አስተዳደር በቸሀ ወረዳ ፋይናንስ ጽ/ቤት**